# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

**የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር፤ በለሚ ኩራ ክ/ ከተማ ጋራ ጉሪ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት**

**አማርኛን በማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ**


በ

ፋንታነሽ ደበበ

አማካሪ

ጌታሁን አማረ (ፐ/ር)


ጥር ፣ 2015

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ፋንታይነሽ ደበበ

# የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር፤ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ጋራ ጉሪ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ

ፅሑፍ ክፈለ ትምህርት

ነሐሴ 2015 ዓ.ም

# የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር፤ በለሚ ኩራ ክፈለ ከተማ ጋራ ጉሪ 7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

ፋንታዬነሽ ደበበ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሑፍ ክፈለ ትምህርት

ለአማርኛ ማስተማር /TEAM/ ኤም. ኤ. ዲግሪ

በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና

ሥነፅሑፍ ክፍለ ትምህርት

ነሀሴ 2015 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር፤ በለሚ ኩራ ክፈለ ከተማ ጋራ ጉሪ 7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በ

ፋንታዬነሽ ደበበ

ነሐሴ 2015 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ

-------------------------- ፊርማ --------------------

ፈታኝ

-------------------------- ፊርማ --------------------

ፈታኝ

-------------------------- ፊርማ --------------------

# ምስጋና

በቅድሚያ ለነገሮች ሁሉ ለረዳኝ ለልዑል እግዝአብሄር ክብር ምስጋና ይግባው። በመቀጠል ለዝህ ጥናት መሳካት ከትልመ ጥናቱ ጀምሮ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ በየጊዜዉ ሳይሰለቹ ስህተቶችን በማረም፣የአሰራር ስልቶችን በመጠቆምና በማበረታታት ክትትላቸዉ ላልተለየኝ አማካሪዬ ፕ/ር ጌታሁን አማረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ከዚህም በተጨማሪ የመመረቂያ ፅሁፉን ለማከናወን የሚያስፈልገኝን በጀት በመመደብ እገዛ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ እንዲሁም ለጥናቴ አጋዥ የሆነ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ የጋራ ጉሪ ትምህርት ቤት መምህራን ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

በመጨረሻም ጥናቴን ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ እስከ ፍፃሜው ድረስ ከጎኔ ሆነው ሲያበረታቱኝ ለቆዩት ለውድ ቤተሰቦቼ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# ማውጫ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ v

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3

1.3. የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 4

1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4

1.5. የጥናቱ ወሰን ........ 5

ምዕራፍ ሁለት

ክለሳ ድርሳናት ........ 6

2.1. አንብቦ የመረዳት ክሂል ምንነት ........ 6

2.2. አንብቦ የመረዳት የመማር ብልሀቶችና አከፋፈል ........ 8

2.2.1. ቀጥተኛ ........ 8

2.2.2. ኢ- ቀጥተኛ ........ 11

2.3. የማንበብ ትምህርት ዓላማ ........ 14

2.4. የማንበብ ትምህርት አስፈላጊነት ........ 15

2.5. የአንብቦ መረዳት ብልሃት አይነቶች ........ 16

2.5.1. ማጠቃለል ........ 16

2.5.2.ማዋሀድ ........ 17

2.5.3. ማዛመድ ........ 17

2.5.4. ምስል ፈጠራ ........ 18

2.5.5. መተንበይ ........ 18

2.6. ጾታና አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች ........ 18

2.7. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 19

ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ዘዴ ........ 22

3.1. የአጠናን ዘዴ ........ 22

3.2. የናሙና አመራረጥ ........ 22

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 23

3.3.1.የጽሁፍ መጠይቅ ........ 23

# አባሪዎች

አባሪ አንድ ለተማሪዎች የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ........................................................................ 57
አባሪ ሁለት ተጠኝ የአማርኛ መምህራኑ እንዲመልሱት የቃል መጠይቅ ........................................ 60
አባሪ ሶስት የፅሁፍ መጠይቁን ተጠኝ ተማሪዎች የመለሱት ድምር ቀጥር ..................................... 61
አባሪ አራት የፅሁፍ መጠይቁን የመለሱት የተጠኚ ተማሪዎች በመቶኛ ስሌት ................................. 65
አባሪ አምስት የተጠኝ ተማሪዎች በሁለቱ ፆታዎች መሀከል ያለውን ልዩነት በመቶኛ ስሌት ............ 69
አባሪ ስድስት በወንዶችና በሴቶች መሀከል ያለውን ልዩነት የጠቅላላ ብልሃቶች መቶኛ ስሌት ............ 71
አባሪ ሰባት ጠቅላላ የተማሪዎች መረጃ ........................................................................................ 72

## የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1. አእምሯዊ ብልሃቶች መረጃ ........ 25
ሠንጠረዥ 2. የትውስታ ብልሃቶች መረጃ ........ 29
ሠንጠረዥ 3. አካካሽ ብልሃቶች መረጃ ........ 32
ሠንጠረዥ 4. ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች መረጃ ........ 37
ሠንጠረዥ 5. ማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ ........ 40
ሠንጠረዥ 6 የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም መረጃ ........ 45
ሠንጠረዥ 7 የሁለቱ ፆታዎች ልዩነት........ 47

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንጻር ምን እንደሚመስል መመርመር ነው። ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን በጥናቱ የተሳተፉት በአላማ ተኮር ናሙና የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ወንዶች 41 ሴቶች 40 ጠቅላላ 81 ናቸው። ከተሳታፊዎች መረጃ የተሰበሰበው በሁለት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ የፅሁፍ መጠይቅና የቃል መጠይቅ ናቸው። የፅሁፍ መጠይቁ አንብቦ የመረዳት ብልሃትን፣ ለመለካት ሲያገለግል ቃለ መጠይቁ ደግሞ ተጨማሪ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆን አገልግሏል። የተሰበሰቡት መረጃዎች በመቶኛ ስሌት ተሰልቶ በገላጭ ምርምር ዘዴ ተተንትነዋል። ስለሆነም አብይ ዓላማውን መሠረት በማድረግ ምርምሬ ከአነብቦ መረዳት ንዑስ ብልሃቶች ውስጥ የበለጠ የሚጠቀሙት የትኛውን እንደሆነ ለማወቅ በመቶኛ ስሌት ተሰልተው ተግባራዊ ተደርጓል። ለዚህም ተማሪዎቹ ስላላቸው የአንብቦ መረዳት አጠቃቀም ከሞሉት የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በአእምሯዊ፣ ትውስታ፣ አካካሽ፣ ልዕለ አእምሯዊና ማህበራዊ በሚሉ አምስት ንዑስ ብልሃቶች ጉልህ ሳይሆን ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል። በተጨማሪነት የታየው ሌላኛው ዝርዝር ዓላማ በሴትና በወንድ ተማሪዎች ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም መኖር አለመኖሩን መፈተሽ ሲሆን በፍተሸው መሰረትም የተሰበሰቡን መረጃዎች በመቶኛ ስሌት በፍተሻው ስሌት ተሰልቶ ወንዶች 22.27 ሴቶች 18.75 በመሆኑ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ አንብቦ የመረዳት አጠቃቀም መኖራቸውን ያመለክታል። በመጨረሻም የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ አስተያየቶችተጠቁመዋል።*

## ምዕራፍ አንድ
## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

አንብቦ መረዳት ፅሁፍን አንብቦ ሀሳቡን የመረዳት፣ የመገንዘብ ተግባር ነው። ከማንበብ ችሎታ፣ ከማስታወስ፣ ትኩረት ከማድረግና ከምክንያታዊነት ችሎታ ጋር ይያያዛል። አንብቦ መረዳት ፅሁፍን በማንበብ አንባቢው ትርጉም ለመመስረት የሚያከናውነው በትኩረት የማሰብ ሂደት ነው (Abdollahi 2010)።

በትምህርት አለም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ከሚያስችሉ ክሂሎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ነው። የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችን ለመማርና ለመረዳት አስፈላጊና ወሳኝ የሆነ ክሂል ነው። በትምህርት ቤት የሚሰጥ ትምህርትን በሚገባ ለመረዳትና ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችል ጠቃሚ ክሂል ነው።

ማንበብ የመቀበያ ክሂል ሲሆን ተማሪዎች ከፅሁፍ የቃላት፣ የሰዋስውና የአረፍተነገር እውቀት የሚቀስሙበት መንገድ ነው። አንብቦ መረዳት የፅሁፉን ዋና ሃሳብና ዝርዝር ሃሳቦች በመለየት በመፅሀፉ የቀረበውን መረጃ የመረዳትና የማወቅ ክህሎት ነው (Al.Ghazo 2015)።

Abdollahi (2010) እንደገለፁት አንብቦ መረዳት ከሁሉም የቋንቋ ክሂሎች በላቀ ደረጃ ለቋንቋ ተማሪዎች እጅግ ጠቃሚ የሆነ ክሂል ነው። ችሎታ ከማንበብ ችሎታ፣ ከትውስታ፣ ከማስተዋልና ከማመዛዘን ችሎታ ጋር የተቆራኘ ነው።

Al.Ghazo (2015) እንዳብራሩት በርካታ ተማሪዎች ከፅሁፍት ዋና ሃሳብን ለይቶ የማውጣት ችግር አለባቸው። እንዲሁም ዋና ሃሳቦችን ተጠቅመው የፅሁፉን መረጃ በአእምሯቸው በማደራጀት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስና የፅሁፉን ሃሳብ ለማብራራት አይሞክሩም። አንብበው መረዳትም አይችሉም።

ንባብ ማለት አንድ ማንበብ የሚችል ሰው በወረቀት፣ በድንጋይ፣ በብራና እና በሌሎችም የጽሁፍ ማስፈሪያዎች ላይ የሰፈረን ሀሳብ አንብቦ በውስጡ የሰፈረውን ፍሬ ሀሳብ መረዳትን የሚገልጽ ሀሳብ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ከጥንት ጀምሮ ንባብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተለያዩ ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል። ንባብ ማለት በጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ምልክቶችን የማየት፣ የመለየት እና የመረዳት ሂደት ሲሆን እነዚህ ምልክቶች ቅንጅት እንዳላቸው መረዳት ጭምር ነው (Williams 1990)።

ልክ እንደ ንባብ ሁሉ ስለ አንብቦ መረዳት ችሎታም የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ለምሳሌ Millar (1982:24) "አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማለት ለአንድ ለተወሰነ ክፍል ደረጃ የሚዘጋጅን የንባብ ክፍል ለክፍሉ የተመደቡ ተማሪዎች ንባብን ያለምንም ችግር አንብበው የንባቡ መልዕክት ምን እንደሆነ የሚለዩበትን ሁኔታ የሚያሳይ ጽንሰ ሀሳብ ነው"ይላሉ፡፡ Smith (1985)& Williams (1993) አንብቦ መረዳትን በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የቀረበን ሀሳብ በጥልቀት አንብቦ የመረዳትን ሁኔታ እንደሚያሳይ ያስረዳሉ፡፡ Smith (1985:24) አያይዘውም አንድን ንባብ አንብቦ መረዳት የሚያስፈልገው ከምንባቡ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ በማሰብ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Nuttall (1982) አንብቦ መረዳት አንድ ጽሁፍ የያዘውን ዋና ፍሬ መረጃ መገንዘብ እንደሆነ ደረጃውም እንደሚለያይ ከገለጹ በኋላ አያይዘውም የሚነበበው ነገር ከሚነበብበት ዓላማ እና ከአነባበብ ዘዴው የተነሳ መለያየት ሊከሰት እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

Grellet (1981) ደግሞ የአንብቦ መረዳት ችሎታዎች በምን ሁኔታ እና ምክንያት የደረጃ ልዩነት ሊኖራቸው እንደሚችል በሚከተለው ሁኔታ በምሳሌ ያስረዳሉ፡፡ በአንድ ሰሌዳ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያ እና በአንድ መጽሄት የታተመ ሳይንሳዊ ጥናት በእኩል ደረጃ ሊነበቡ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የተለጠፈው ማስታወቂያ በገረፍታ ተነቦ የሚፈለገው ፍሬ ነገር ብቻ የሚያዝ ሲሆን በመጽሔት የታተመው ጥናታዊ ጽሁፍ ግን ጥልቅ የሆነ ንባብ ይደረግበታል፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያ የገረፍ ገረፍ ንባብ ሲሆን ሁለተኛው ጥልቅ ንባብ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አንብቦ መረዳትን ጠቅለል ባለ ሁኔታ በሁለት ከፍሎ መመልከት እንደሚቻል ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ከእነዚህ ምሁራን መካከል Grellet (1981)& Sheng (2000) በማለት ይገልፃሉ አንድን ጽሁፍ አንብቦ ፍሬ ሀሳቡን መረዳት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በጽሁፍ ውስጥ የሰፈሩትን ዋና ዋና ሀሳቦችን መረዳት፣ በግልጽ የሚታዩ ሁነቶችን መለየት እና መረዳት፣ የድርጊቶችን የጊዜ እና የሁኔታ ቅደም ተከተል፣ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ልዩነቶች እና አንድነቶች ምክንያት እና ውጤቶች ወዘተ. መረዳት ከአንባቢው ይጠበቃል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ንባቡን አንብበው ከጨረሱ በኋላ በምንባቡ ውስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ነጥቦች ከምንበቡ አንጻር የሚገምቱበት ነው፡፡

አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች የሚባሉት በሁለት የሚመደቡ ሲሆን የመጀመሪያው ርዕቱ የመማር ብልሃቶች በመባል ይታወቃሉ፡፡ በስሩም የትውስታ ብልሃቶች አዕምሮታዊ ብልሃቶች እና፣ አካካሽ ብልሃቶች የሚባሉትን በዋናነት ይይዛል፡፡ ሁለተኛው ኢ-ርዕቱ የመማር ብልሃቶች የሚባሉ ሲሆን በስሩ የስሜት ነኪ የቁጥጥር ብልሃቶች፣ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሃቶች እና የማህበራዊነት ብልሃቶች የሚባሉ ርዕሰ ጉዳዮች ይገኙበታል፡፡ Oxford (1990) ቋንቋን የመማር ብልሃቶች፣O'Malley&

Charnot (1995) የመማር ብልሃት እንዲሁም የተማሪው ብልሃቶች በማለት ሰይማዋቸዋል፡፡ Armbruster& Osborne (2002) የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች መስፈርት ያሟሉ ብለው ያሰፈሯቸው ማጠቃለል፣ ማዋሀድ፣ ምስል ፈጠራ፣ ማዛመድ እና መተንበይ ናቸው፡፡

ጥናቶች በሴቶችና በወንዶች መካከል በአንብቦ መረዳት ዙሪያ ሰፊ የጾታ ልዩነት አለ በማለት ያመለከቱት በፊላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ልዕለአእምሮዊ የማንበብ ብልሃት ትኩረትን የሳበ ጉዳይ ሆኖ ቀርቧል (Iwai 2011)፡፡ «ልዩነት አለ ይኸውም፤ የ15 ዓመት እድሜ ባላቸው ተማሪዎች ላይ የተደረገው የናሙና ጥናት እንደሚያስረዳው 60% የሚሆኑት ሴቶች ከወንዶቹ ይልቅ የተሰጣቸውን ምንባብን አንብቦ በመረዳት የተሻለ ተሞክሮ እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡ የልዩነቱ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደውም ሴቶች ንባብን የሚያፈቅሩ ሆነው መገኘታቸውንና ለንባብ በቂ የሆነ ጊዜን መስጠት በመቻላቸው ነው» (Cromley 2005 195-199)፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ተማሪዎች አንብበው የሚረዱባቸው ብልሃቶች ላይ ነው፡፡ ትኩረቱም በጋራ ጉሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም የሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ብልሀት አጠቃቀም ከፆታ አንፃር መፈተሽ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ሳይንስና ቴክኖሎጂ በተስፋፋበት ወቅት አንብቦ የመረዳት ክሂል እንደ መሰረታዊ ፍላጎት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ በDechant and Smith (1987) ገለፃ ተማሪዎች በመጀመሪያዎቹ ክፍሎች አንብቦ የመረዳት ክሂላቸው በደንብ ከዳበረ በኋለኞቹ አመታት በጣም ስኬታማ ይሆናሉ፡፡ Hansen (1992) ባደረጉት ጥናት ተማሪዎች የመፃፍ ክህልን በትምህርት ቤት የሚማሩትና የሚተገብሩት ሆኖ ሲሰማቸው ማንበብን ግን በቤታቸው በመተግበር የሚማሩት እንደሆነ አድርገው እንዲያስቡ የሚያደርግ የማስተማር አውድ መዘውተሩን አሳይተዋል፡፡ የክፍል ውስጥ ትምህርቱ በአብዛኛው በመምህራን ብልሀት አልባ የማስተማር ተግባር በመሸፈኑ ተማሪዎች ትምህርትቤት ማንበብን ለመማር ትክክለኛው ቦታ ሆኖ እንዳይሰማቸው እንዳይደረግ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡

አጥኚዋ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አጠቃቀም/ ከፆታ አንፃር/ ጥናት በኢትዮጵያ አውድ የተሰጠውን ትኩረት ለማወቅም በማንበብ ክሂል ላይ የተካሄዱ ጥናቶችን ከልሳለች፡፡ ከእነዚህም ጥናቶች የተወሰኑት የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ በመዳሰስ ላይ (ማስተዋል 1989፣ ተስፋዬ 2001)፣ ለችግሩ ስነ ትምህርታዊ መፍቴዎችን በማፈላለግ ላይ ያተኮሩትንም ቢሆኑም (እንግዳ 1992፣ ጌታቸው 1991፣ ግሩም 2003) አብዛኛዎቹ የተለያዩ አንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ሞዴሎችን ተግባራዊነት በመፈተሽ ላይ ያተኮሩ እንጂ የአንብቦ መረዳት ብልሀቶችን አጠቃቀም ከፆታ አንጻር

አልፈተሹም።በፅሁፉ ውቅር ላይ ደግሞ (ጥሩነሽ 2005) ስለሆነም አንብቦ የመረዳት ብልሀቶች አጠቃቀም ከፆታ አንጻር ምን ውጤት ሊያመጡ እንደሚችሉ ጥናት መደረግ እንዳለበት አጥኚዋ ታምናለች።

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በየትኛው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም የተሻሉ እንደሆኑ ለማወቅ ባላት ፅኑ ፍላጎት የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር ምን እንደሚመስል በመፈተሽ ልዩነቱን ለማወቅና የመፍትሄውን ሃሳብ ለመጠቆም ነው። እንዲሁም አጥኚዋ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማድረግ ያነሳሳት መሰረታዊ ችግር ባስተማረችበት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀማቸው በሁለቱ ፆታ መሀከል ያለው ልዩነት እና በአጠቃቀማቸው ዝቅተኛ መሆኑ ያሳስባት ስለ ነበር ነው። በዚህም ላይ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ብልሃት ከፆታ አንፃር ለማሳደግ በየጊዜው የሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ለውጥ ባለማምጣታቸው አብዛኛዎቹ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃት ዝቅተኛ ስለ ሆነ ችግሩን ከስር ለመፍታት ታስቦ ወደ ጥናት ተገብቷል።

## 1.3. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጋራ ጉሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም የሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ብልሀት አጠቃቀም ከፆታ አንፃር መፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት።

1. ተማሪዎች የበለጠ የሚጠቀሙት የትኞቹን የአንብቦ መረዳት ብልሀት እንደሆነ መለየት፣
2. በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም መኖር አለመኖሩን መፈተሽ፣

## 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት የሚታዩ ብልሃቶችን መለየት ለመማር ማስተማሩ ሂደት የላቀ አስተዋፅኦ ያበረክታል። ከዚህም በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉት ስነትምህርታዊና ምርምራዊ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

1. ተማሪዎች በአብዛኛው የትኛውን የአንብቦ መረዳት ብልሀት አጠቃቀም ብቃታቸውን ለማሳየት ይችላል።
2. ለመምህራን የተማሪዎቻቸውን የንባብ ብልሀቶች ምርጫ በመለየት የትምህርት አቀራረባቸውን፣ የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎቻቸውንና የማስተማር ዘዴያቸውን በጥሩ

ሁኔታ እንዲያዘጋጁና ዝንባሌያቸውን መሰረት በማድረግ የሚመርጧቸውን የንባብ ብልሀቶች በመለየት ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ፍንጭ ይሰጣል፡፡

3. ለተመራማሪዎች ወደፊት ከአንብቦ መረዳት ብልሀት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ምርምሮችን ለሚያደርጉት ተመራማሪዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከአራቱ የአማርኛ ቋንቋ ክህሎች ውስጥ በአንዱ የአንብቦ ክሂል ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ሂደቱም አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከጾታ አንፃር መፈተሽ ላይ ያተኮረ ሲሆን፡፡ ይህ ጥናት በትምህርት ቤቱ ከሚማሩት ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ስምንተኛ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ በ2015 ዓ.ም የሚማሩ የ7ተኛ ክፍል ተማሪዎች ተመዝግበው ትምህርታቸውን ሲከታተሉ በነበሩ ተማሪዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1. አንብቦ የመረዳት ክሂል ምንነት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት /1999፣279/ "ንባብ በፅሁፍ ላይ የሰፈረን ነገር በአንደበት ወይም በድምፅ አማካይነት ጮክ አድርጎ ማንበብ፣ የመናገርና የመስማት ድርጊት፣ በቤተ-ክህነት ትምህርት ቤት ከውርድ ንባብ ቀጥሎ የሚሰጥ የአነባበብን ጥራትና ፍጥነትን የሚመለከት ትምህርት ነው"በማለት ይፈታዋል፡፡ 'አነበበ' የሚለውን ቃል ደግሞ "በፅሁፍ ላይ የሰፈረን ነገር ድምፅ እያሰማ በአንደበቱ አለ፣ ተናግረው ወይም ድምፅ ሳያሰማ በአዕምሮው ዘለቀው "ይለዋል፡፡ ንባብ በፅሁፍ ወይም በህትመት ለቀረቡ ቃላት እውቅና በመስጠት ፍቻቸውን የመረዳት ሂደት ነው፡፡ይህ ፍች እንደሚያመለክተው ንባብ ቃላትን ከመረዳት የሚጀምር መሆኑን ነው፡፡

ማንበብ ከመቀበያ ክሂል አንዱ ነው፡፡ ዋና ዋና ተግባራቱም የሚከተሉት እንደሆኑ Harmer (2001፡45) ያስረዳሉ፡፡ ከፅሁፍ ውስጥ ፍሬ ሃሳብን ለይቶ ለማውጣት፤የፅሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ ለመረዳት፣ የፅሁፍን የሀሳብ ፍሰት ለማወቅ፣ የአንቀፅ አወቃቀርና አደረጃጀት ለመለየት፤ የቃላትን አውዳዊ ፍቺዎች ለመገንዘብ እና የፃሀፊውን ሀሳብ ለመረዳት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ንባብ በግል የሚከናወን ተግባር ከመሆኑም ባሻገር በጊዜ እና በቦታ ተወስኖ የሚገኝን ፅሁፉ መልዕክት በመረዳት ምላሽ ለመስጠት የምንሞክርበት አእምሮአዊ ተግባር ነው (Davies 1995):: Alfassi (2004) and Wei (2005)አንድን ፅሁፍ ለማንበብ የማንበብ ችሎታ መዳበር ወሳኝ እንደሆነ ከገለፁ በኋላ በመማር ማስተማር ሂደትም የትኛውም የትምህርቱን ይዘት ለመረዳትም ሆነ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ማንበብ መቻል እና መረዳት አስፈላጊ እንደሆነ ያሥገነዝባል፡፡ አያይዞም በተለይ አሁን ባለንበት ዘመን መረጃዎችን ከድህረ ገፅ፣ ከመፅሄት እና ከተለያየ መፅሀፍት አንብቦ ለመረዳት ለተረዱት ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት የተማሪዎች የማንበብ ክህሎት እና ብልሀት ተማሪዎች በሚያሥመዘግቡት ውጤት ላይ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ እንዳለው ያሥረዳል፡፡ አንብቦ መረዳት የማንበብ ክሂል ትምህርትን ለማዳበር አስፈላጊ ነው፡፡ "ንባብም ሕይወት አለው" ብለን የምናስበው ተማሪው ለዚህ ስኬት በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ በሚያገኘው ውጤት አማካኝነት ነው፡፡ ይህን በማስመልከት Alfassi (2004) and Wei (2005) የሚከተለውን ይላሉ፡፡ የሚያነቡት ፅሁፍ ውስጥ ክህሎትን ማዳበር የሚችሉ፣ የተለያዩ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሀቶችን የሚጠቅሙ፣ የሚያነቡበትን ዓላማ የሚረዱ እና በንባብ ክሂል ያገኙትን አዲስ መረጃ ከቅድመ እውቀታቸው ጋር አስማምተው ጉዳዩን የሚገነዘቡ ናቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Ratna (2014) ንባብ መጠነ ሰፊ ሚና ያለው፣ እውቀታችን ውስን እንዳይሆን እና በአለም ላይ ያሉ የተለያዩ ነገሮችን እንድናውቅ የሚጠቅመን ክሂል እንደሆነ ያሥረዳሉ፡፡ የማንበብ ችሎታ ሌሎች ትምህርቶችን በመማር ችሎታ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በንባብ ጊዜ ተግባራዊ የሚሆኑ የመማር ብልሀትን መጠቀም ስንችል ነው፡፡ ክሂልን የመማር ብልሀት የቋንቋ መማር ብልሀት አንዱ ነው፡፡ የማንበብ ብልሀትም ከክሂል መማር መካከል ይካተታል፡፡

እንደ Nuttall (1996) አገላለጽ አንብቦ መረዳት የፅሁፍን ቅደም ተከተላዊ፣ የዓረፍተ ነገሮችን የሀሳብ ግንኙነት እና ግጥምጥምነት የሚፈጥሩ አያያዦች እና የፅሀፊው ሀሳብ የሚንፅባረቅባቸው በመሆናቸው ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡ አያይዘውም አንድን ፅሁፍ በመረዳት ሂደት በፅሁፍ ውስጥ የሚገኙ አረፍተ ነገሮችን አገልግሎታዊ ዋጋ መረዳት ተገቢ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ Grellet (1981) የተባሉ ፀሀፊ ደግሞ ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ አንብበው ለመረዳት ከተለያዩ የአደረጃጀት ዘዴዎች ጋር መተዋወቅ እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ፅሁፍን ለማንበብ በሚዘጋጅበት ጊዜ የፅሁፉን አደረጃጀት በመለየት ምን አይነት ታሪክ ወይም ሀሳብ ሊመጣ እንደሚችል መገመት እንደሚችሉ እድል እንደሚፈጥርላቸው ያስገነዝባሉ፡፡

እንደ Grellet (1981) አገላለፅ አንብቦ መረዳት መቻል ማለት ከአንድ አሃድ ውስጥ ተፈላጊውን መረጃ በብቃት ማሰባሰብ መቻል ማለት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት ውስጥ አንባቢው የማይፈልገውን መረጃ እያንጓወለለ በመተው የሚፈልገውን ዓይነት ብቻ ሲመርጥ በብቃት የሚገነዘብበትም ሁኔታ የሚጠቃለለው እዚሁ ውስጥ ነው፡፡

ከሐሳቡ መረዳት የሚቻለው አንብቦ መረዳት ማለት ተፈላጊ የሆነውን መረጃ ለመምረጥ አስፈላጊውን ትኩረት ለማሳረፍ መቻል እንደሆነ ነው፡፡ አንባቢው ተፈላጊ ነጥቦችን ብቻ በመለየት እንዴት ማንበብ እዳለበት ካወቀ አንብቦ በመረዳት ረገድ ችግር አይገጥመውም ማለት ነው፡፡

ስለ ብልሃት Davies (1995:50) ሲገልጹ «ብልሃቶች ውህድ አሀድን ለመረዳት ወይም መረዳትን ለማቀላጠፍ ዓላማ ሲባል ጥቅም ላይ የሚውሉ አካላዊ ወይም አእምሮኣዊ ምላሽ ናቸው» ይላሉ፡፡

አጠቃላይ አንብቦ መረዳት ሲባል አንድ ሰው አንድን የተፃፈ ነገር ወይም ፅሁፍ አንብቦ በመረዳት ጸሀፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ጉዳይ የመረዳትን ሂደትን የሚገልፅ ጽንሰ ሀሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ብልሃቶች ደግሞ የመማር ችግሮችን ለመፍታት ወይም መማርን ለማቀላጠፍ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የምንጠቀምባቸው ዝርዝር ዘዴዎች ናቸው፡፡ ስለ ብልሃቶች ምንነት በጥልቀት ለመረዳት

ማንበብን የመማር ብልሃቶች መለያ ባህሪያቸውን መፈተሽ አስፈላጊ ነው። ብልሃቶች በግንዛቤ ደረጃ፣ በማዛመድ ደረጃና በቅጽበታዊ የክንውን ደረጃ ላይ ሊከሰቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ያሻል።

## 2.2. አንብቦ የመረዳት የመማር ብልሀቶችና አከፋፈል

ስለ መማር ብልሀቶች ምንነት የተለያዩ የየራሳቸውን ብያኔ ይሰጣሉ። የማንበብን ብልሃቶች አንባቢዎች አንድን ሥራ እንዴት እንደሚረዱ፣ ምን ዓይነት ጽሁፎችን እንደሚያነቡና እንዴት እንደሚያነቡ ይጠቁማል። ለምሳሌ አስቸጋሪ የሆነውን ክፍል እንደገና ማንበብ፣ የማይታወቁ ቃላትን ከጽሁፍ አውድ መረዳት፣ የአነበቡትን ጽሑፍ ማጠቃለል እና የአንባቢውን የቀደመ እውቀት ማወቅ ወዘተ. እንደሚያስፈልግ Carrell et al. (1989) ያስረዳሉ። ተገቢ የሆነ ማንበብን የመማር ብልሃት መማር ከፍ ያለ በራስ መተማመንን ለመፍጠር ያስችላል።

Oxford (2003) ማንበብን የመማር ብልሃቶች የቋንቋ ተማሪዎች በማንበብ ትምህርት ሂደት የንባብ ተግባራትን ለማካሄድ የሚገለገሉባቸው ክንዋኔዎች፣ ልምዶች ወይም ስልቶች ሲሆን፣ እነዚህም ማንበብን የመማር ብልሃቶች በእያንዳንዱ ግለሰብ አእምሮ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የአሰራር ጸባዮች እንደሆኑ ያሥረዳሉ።

Oxford (1990) ቋንቋን የመማር ብልሃቶች፣O'Malley and Charnot (1995) የመማር ብልሃት እንዲሁም የተማሪው ብልሃቶች በማለት ሰይማዋቸዋል። Oxford (1990) እንደገለፁት የማንበብ ብልሀት አከፋፈል በሁለት መልኩ ሲሆን ይኸውም ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ በማለት ነው።

### 2.2.1. ቀጥተኛ

ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ማለት የቋንቋ ትምህርትን የመማር ማስተማር ሂደት ቀላል ለማድረግ በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የሚከናወኑትን ልዩ ልዩ የቋንቋ ማስተማሪያ ተግባራትን የሚያግዝ ዘዴ ነው። Oxford (1990) ቀጥተኛ የመማር ብልሀቶች ቋንቋን የሚማሩ ተማሪዎች ቀጥተኛ በሆኑ ጉዳዮች መነሳት እንዳለባቸው ያስረዳሉ። ርዕሰ ጉዳዮቹም የትውስታ ብልሀቶች፣ አዕምሮታዊ ብልሀቶች እና አካካሽ ብልሀቶች ናቸው። እነዚህ ነጥቦች ከዚህ በማስከተል ስለምንነታቸው እንመለከታለን።

#### 2.2.1.1. የትውስታ ብልሃት

የዚህ አይነት ብልሀቶች ትኩረታቸው ከተማሪዎች የማስታወስ ብቃት እና ብልሀት ጋር የተቆራኘ ነው። በመሆኑም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያገኙትን እውቀት የረጅም ጊዜ እና የአጭር ጊዜ ትውስታ ውስጥ በመመዝገብ እና በተፈለገ ጊዜ በአእምሮው የመዘገበውን እውቀት አስታውሶ የሚጠበቅበትን ሂደት የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ ነው። O'Malley& Charnot (1995)

ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ብልሀቶች መጠቀም እንደሚገባቸው ይመክራሉ፡፡

1. ተማሪዎች በአንድ ወቅት የተማሩትን ትምህርት በጊዜ ሂደት ሊዘነጉት ወይም ሊረሱት ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ይህ እናዳይፈጠር ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በየጊዜው መከለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ለአንድ ነገር ምላሽ ከሚሰጥባቸው አኳኋኖች መካከል አካላዊ ምላሽ ዘዴ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ለአንዳንድ ጉዳዮች ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ያገኟቸው ዕውቀቶች እና ፅንሰ ሀሳቦች እንደየ ባህሪያቸው መማደራገጀት እና በማዋቀር መማር ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ የሚማሩትን የቋንቋ ትምህርት እውቀት ከዚህ በፊት ከሚያውቁት መረጃ ጋር በማጣመር የበለጠ እውቀታቸውን ማዳበር ያስፈልጋቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ዘዴ የሚጠቅመው አንድን የተፃፈ ነገር ለማስታወስ፣ ለማከማቸትና በጥልቀት እንዲቆይ ለማድረግ ነው፡፡

### 2.2.1.2. አዕምሮታዊ ብልሃት

አእምሮኣዊ የማንበብ ብልሃት እንደ ቋንቋ መማር ብልሃት እንደሆነ፤ ተማሪዎቹም ይህንን ብልሃት ተግባራዊ ቢያደርጉ በትምህርታቸው የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆኑ እና እንዲሁም በዚህ ብልሃት ስር የተለያዩ ንዑሳን ብልሃቶች እንደሚካተቱ Oxford (1990) O'Malley& charnot (1995) ያስረዳሉ፡፡ Salovaara (2005) ደግሞ አእምሮአዊ ብልሀቶች ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ በቀጥታ በመጠቀም ተረድተው የሚማሩበት የብልሀት አይነት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ እኚህ ምሁር አያይዘውም ተማሪዎች ያተኮሩበትን ቋንቋ ይዘት ሲማሩ ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት እንዲሰጡ ያስገነዝባሉ፡፡

1. ይዘቶችን በመደጋገም፣ የቋንቋውን ህጎች እና ቀመሮችን በማውጣት ማጥናት፣ መለማመድ እና በሚማሩት ቋንቋ መገልገል፣
2. በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ በዋናነት ሊታለፍ የተፈለገውን መልዕክት ለመረዳት ይቻላቸው ዘንድ ለትምህርት ይዘቱ ዋና ርዕሰ ጉዳይ የተለየ ትኩረት መስጠት፤
3. የሰዎች የቋንቋ ችሎታ የተለያየ በመሆኑ ተማሪዎች የራሳቸውን የቋንቋ ችሎታ ከሌሎች ሰዎች ጋር በማወዳደር የቋንቋ ችሎታቸውን መለካት እና

4. የተለየዩ የቋንቋ መማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የቋንቋ ችሎታቸውን እና የመረዳት አቅማቸውን ለማዳበር መጣር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

አዕምሮዊ የመማር ብልሃቶች ሲወሱ አእምሮአዊ የማንበብ አስተሳሰቦች አበረው ይውላሉ፡፡የተለያዩ የንባብ ንድፈ ሀሳቦች አንብቦ በመረዳት ውስጥ ያለውን ሂደት በተለያየ መንገድ ለመግለጥ ሞክረዋል፡፡ ስኬታማ የንባብ ልምድ እንዴት ሊመጣ እንደሚችል ወይም አንብቦ በመረዳት ውስጥ ያለውን ሂደት ውስጥ ሊያጋጥም የሚችልን ችግር ለመመልከት ሞክረዋል፡፡ አእምሮአዊ የማንበብ ንድፈ ሀሳቦች ንባብን የሚመለከቱት ፍፁም አእምሮአዊ ሂደት አድርገው ነው፡፡ አስቀድሞ በ1980ዎቹ ንባብ ሌሎች ውጫዊ እንቅስቃሴዎችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ማህበራዊ እንቅስቃሴ ተከር ተደርጎ ይታይ ነበር፡፡

### 2.2.1.3. አካካሽ ብልሀቶች

አካካሽ ብልሃቶች ተማሪዎች በማንኛውም ሁኔታ የቋንቋ እውቀቱ በቂ ሆኖ ባልተገኘበት የተግባቦት ሂደቱ እንዳይቋረጥ እና እንዲቀጥል የሚያስችል ብልሀት ነው፡፡ ይህ ብልሀት አንደ Sumaira (2014) አገላለፅ ደረጃዎች አሉት፡፡ እነሱም፦ ቃላትን መለየት፣ የመተካካት ብልሃት እና የማዛመድ ብልሃት ናቸው፡፡

1. ቃላትን የመለየት ብልሃት ትኩረቱ ቃላት ምን እንደሆኑ ማወቅ ሲሆን ጥናቱ ምን ላይ እንደተመሰረተ የማንበብ ብልሃቱ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተም መገንዘብ ነው፡፡

2. የመተካካት ብልሃት ደራሲው በመፅሀፉ ያላካተተውን ጉዳይ አንባቢው ክፍተቱን የሚሞላበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ ማለት በደራሲው ያልተቀመጠን ዐረረፍተ ነገርና ያልተካተተን ጉዳይ በአንድ ላይ ማካተት ነው፡፡

3. የማዛመድ ብልሃት የሚገልፀው አንባቢው ፀሀፊው ከገለፀው በላይ ማወቅን ሆኖ ያነበበውን ነገር ከቀደመ እውቀቱ ጋር ማስተሳሰርን ነው፡፡

እንደ Ozek & Civelek (2006) አገላለጽ የተግባቦት ሂደቱ እንዳይቋረጥ እና እንዲቀጥል ለማድረግ የሚከተሉትን ክንውኖች መከናወን አለባቸው፡፡

1. ብልሃት የተሞላበት እና እውቀትን መሰረት ያደረገ ግምት ለመስጠት መሞከር

2. ስነ ልሳናዊ ያልሆኑ ወይም አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመመልከት ፍቺ ለመስጠት መሞከር፤ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ የሚተላለፍን ሀሳብ ለመረዳት ለሚያሠናክሉ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት ለመፍታት መጣር፤
3. ስሜትን በተለያየ መንገድ ለመረዳት እና ለመግለፅ የተለያዩ ዘዴዎችን በመፍጠር መለማመድ፤ እና ሃሳብ ተቀባይነት የሚያገኘው በመረጃ ሲደገፍ በመሆኑ ጽሁፍም ሆነ በንግግር የሚተላለፍ ሀሳብን በመረጃ ለማስደገፍ መሞከር የሚሉት የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

2.2.2. ኢ- ቀጥተኛ

ኢ- ቀጥተኛ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች የትምህርቱን ሂደት እንዴት ማስኬድ እንዳለባቸው የሚጠቁም ሂደት ከመሆኑ በተጨማሪም የመማር ማስተማሩ ሂደት ዓለማ እና እቅድ የሚነደፍበት፣ ሁኔታዎች የሚመቻቹበት ሂደት ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ልዩ ልዩ የመማር ማስተማር ዘዴዎች ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡበት የብልሃት አይነት እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይህ የመማር ብልሃት በስሩ የስሜት ነኪ የቁጥጥር ብልሃት፣ ልዕለ አዕምሮታዊ ብልሀት የሚባሉ ንዑሳን ርዕሰ ጉዳዮች ያቀፈ ነው፡፡ በመሆኑም ስለነዚህ ነጥቦች ምንነት ቀጥለን በጥቂቱ እንመለከታለን፡፡

2.2.2.1 የስሜት ነኪ የቁጥጥር ብልሃት

የስሜት ነኪ የቁጥጥር ብልሃት ተማሪዎች መማር ማስተማር ሂደቱ የሚያድርባቸውን የመፍራት እና የመጨነቅ ስሜት፣ ጥሩ ያልሆነ አመለካከት እና ዝንባሌ ለመቆጣጠር የምጠቀምበት ብልሃት ነው፡፡ እንደ Oxford (1990) አገላለፅ መጥፎ ስሜት፣ የመማር ማስተማር ሂደትን ያደናቅፋል፡፡ በተቃራኒው ጥሩ ስሜት ደግሞ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚሰማቸውን ጥሩ ያልሆኑ ስሜቶች መቆጣጠር በመቻል የተካኑ ናቸው፡፡ Oxford (1990:140-141) አያይዘውም ተማሪዎች በሚማሩበት ወቅት የሚያሰናክሏቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

1. መጥፎ ስሜት የመረዳት ችሎታን ስለሚያዛባ ወደ መማር ማስተማሩ ሂደት ሲገባ ምንም የተፈጠረ ጥሩ ያልሆነ ሁኔታ መፈጠሩን መርሳቱ ወይም ትኩረት አለመስጠት፤
2. የተለያዩ የራስን ሞራል የማይጎዱ ሁኔታዎችን ድክመት መቀበል፡፡ እንዲሁም በተቻለ አቅም የሚሰራው ስራ ውጤታማ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴዎችን ራስን ማበረታታት፤
3. በመማር ማስተማር ሂደት የሚፈጠርን ውጥረት የተለያዩ ዘዴዎችን ራስን ለማዝናናት እና ከጭንቀት ለመውጣት መጣር፤ እና

4. በመማር ማስተማርም ሆነ በማንኛውም ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቋቋም መሞከር፣ ችግርን ለአቻ ወይም ለሌሎች ሰዎች ለመጋራት መሞከር፣ ችግሮችን በንቃት በመከታተል መፍትሄ ለመፈለግ መጣር የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 2.2.2.2 ልዕለ አእምሯዊ ብልሃት

ልዕለ አእምሯዊ ቃልን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት አሜሪካዊው Flavell (1978) ነው፡፡ ይህ ተመራማሪ ቃሉን ለመጀመሪያ ጊዜ በመጠቀም ለአለም አስተዋውቋል፡፡ እውቀትን 'Meta' ከሚለው የግሪክ ስረው ቃል ጋር አንድ ላይ በማድረግ ልዕለ አእምሯዊ የሚለውን ትርጉም እንዲይዝ አድርጓል፡፡ የቃሉ ትርጉም ለመረዳት ሲባል የሚደረግ ፍኖተ አእምሮ ማለት ሲሆን ስለ ማሰብ የሚደረግ ፍኖተ ሀሳብ ማለት ነው (Flavell 1978)::

እንደ Flavell (1978) ትርጉም ልዕለ አእምሯዊነት የሚመለከተው አንድ ሰው በአእምሯዊ ሂደት ውስጥ ሊኖረው የሚችለውን እውቀት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንድ አንባቢ ራሱን አእምሯዊ ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚጓዝባቸው ሂደቶች ከልዕለ አእምሯዊነት ጋር ተዋህደው መረዳትን ወደተሻለ ደረጃ ማድረስ የሚችሉ ናቸው፡፡

ልዕለ አእምሯዊ የማንበብ ብልሀት የምርምር ሥራዎች እንዲበረታቱ ማድረግ ችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አዳዲስ ተመረማሪዎችን ወደ ዘርፉ የጠራ የምርምር ዘርፍ ነው፡፡ ልዕለ አእምሯዊ የማንበብ ብልሃትን በሁለት ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ የመጀመሪያው በአንባቢያን ጥቅም ላይ የሚያተኩር ሁለተኛው አንባብያን የሚጠቀሙበት አእምሯዊ የሆኑ ክህሎችን የሚያበረታቱ ብልሀት ናቸው፡፡ በልእለ አእምሯዊ ብልሀት የማንበብ ብልሀት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ይህ ክፍፍልም ቅድመ ተከተልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ እነዚህ ስልቶች ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ፣ ድህረ ንባብ ያለውን ሁኔታ ይመለታሉ፡፡ ከንባብ አስቀድሞ አንባቢው ልዕለ አእምሯዊ ብልሀት ሊጠቀም ይችላል፡፡ በንባብ ጊዜ አንባቢው የንባብ ፍጥነቱን በሚያውቀው ነጥብ ዙሪያ ላይ በማፍጠን አዳዲስ በሆኑ ነገሮች ዙሪያ ዝግ እና ምንባቡን የራሱ አካል በማድረግ የሚረዱበትን የብልሀት ዘዴ ይዘይዳል፡፡ ድህረ ንባብ አንባቢው ያነበበውን ምንባብ ከቀደመ እውቀቱ ጋር ያዛምዳል፡፡ ድህረ ንባብ አንባቢው ያነበበውን ምንባብ ከቀደመ እውቀቱ ጋር ያዛምዳል፡፡

ልዕለ-አእምሯዊ ብልሀት ተማሪዎች በራሳቸው የሚማሩበትን መንገድ የሚያስተካክል ሲሆን እውቀትን እና የግንዛቤያችንን ሂደት የሚቆጣጠር ነው (Oxford 1990):: ከዚህም ሌላ Papaleontious-Louca (2003) ልዕለ-አእምሯዊ ብልሀት ሁሉንም የግንዛቤ ደረጃ እነዚህም በራስ

አስተሳሰብ ስለ አንድ ነገር የሚሰማን፣ ስለ አንድ ነገር ማሰብ በመከታተል እና በመቆጣጠር ምላሽ መስጠትን እንደሚያካትት ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Oxford (1990) ልዕለ-አእምሯዊ የንባብ ብልሀት ስድስቱ የንባብ ብልሀቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ተምሪዎች እቅድ ለማውጣት፣ ለማዘጋጀት እና ትምህርታቸውን ለመገምገም ይህ ብልሀት ተስማሚ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም እነዚህ ብልሀቶች ቀጥተኛ ትኩረት እና እራስን በራስ መገምገም፣ ማደራጀት፣ ግቦችን እና አላማዎችን ማዘጋጀት እና ለልምምድ እድሎችን መፈለግን የሚያካትቱ ሲሆን በንባብ አውድ ውስጥ ራስን በራስ መቆጣጠር እና ማረም የዚህ ብልሀት ተጨማሪ ምሳሌዎች እንደሆኑ ምሁሩ አክለው ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ልዕለ-አእምሯዊ ብልሀት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት አሉት፡፡

1. የተሰጣቸውን የተለያዩ የንባብ ተግባራትን በራሳቸው እንዲያከናውኑ ማድረግ፣
2. የማንበብ ተግባራትን በሚያከናውኑበት ወቅት ምን ምን አይነት አንብቦ የመረዳት ብልሀቶችን መጠቀም እንዳለባቸው፣
3. የተጠቀሙባቸው የተለያዩ የማንበብ ብልሀቶች የሚፈልጉት ግብ ላይ ማድረስ መቻላቸውን ወይም አለመቻላቸውን  ተግባራቶቹን የሚመረምሩበት፣
4. ተማሪዎቹ ራሳቸውን በመቆጣጠር ምንባቡን እንዲያነቡ እና ለምን እንደሚያነቡ ራሳቸውን በመጠየቅ ተግባራቶችን እንዲያከናውኑ የሚያደርጋቸው ነው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 2.2.2.3. የማህበራዊ ብልሃት

የማህበራዊነት ብልሃቶች ትኩረት ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርታቸውን ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተባበር የሚማሩበትን ሂደት የሚያሳይ የኢ-ቀጥተኛ ብልሃት አይነት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ተግባራት ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ የሚመሩበት እንዲሁም መምህራቸውን እና በሚማሩት ቋንቋ በቂ እውቀት ያላቸው ሰዎችን ጠይቀው የሚረዱበት ሂደት ነው፡፡ ተማሪዎች ይህን በሚያደርጉበት ወቅት ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ሰጥተው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡

ማህበራዊነት መፍጠር፦ ይህ ማለት ተማሪዎች በትምህርትም ሆነ በመኖሪያ ቤት አካባቢ ለሚኖሩ እና ስለተተኳሪው ቋንቋ በቂ እውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የቋንቋ ችሎታውን

ለማዳበር መጣር እና ተማሪዎች የመረጡትን ቋንቋ ሲማሩ ወይም ሲለምዱ በቋንቋ ዙሪያ በቂ እውቀት ያላቸውን ሰዎች ገለፃዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የቋንቋ ችሎታውን ለማዳበር መጣር አለባቸው፡፡ በማህበራዊ ብልሀት ስር የሚካተቱት ንኡሳን ብልሃቶች ጥያቄ መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር እና ሌሎችን ማዳመጥ ናቸው፡፡

ሀ. ጥያቄ መጠየቅ፦ ጥያቄ መጠየቅ ዋነኛው ማህበራዊ የማንበብ ብልሃት አካል ነው፡፡ ጥያቄ መጠየቅ ተማሪዎች ትክክለኛው ትርጉም ለማንገኘት እና ለመገንዘብ የሚረዳቸው ነው፡፡ ተማሪዎች ከመምህራቸው፣ ከአቻዎቻቸው ጋር እርስ በእርስ በመነጋገር በታላሚው ቋንቋ ሰፋ ያለ ግበዓት በማግኘት የመማር ፍላጎታቸው እና ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

በዚህ ብልሃት ሌላን ሰው መጠየቅ (ለምሳሌ መመህርን ወይም በታላሚው ቋንቋ አፉን የፈታ ወይም የበለጠ ብቃት ያላቸው ተማሪዎችን (3ደኛ) መጠየቅ እና ራስን መጠየቅ ነው፡፡ በተለይ ራስን መጠየቅ ተማሪዎች ፅሁፍን አንብበው ካጠናቀቁ በኋላ ያነበብኩት ምን ያህል ገብቶኛል እያሉ ራሳቸውን የሚጠያቁበት ነው፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን ሲጠይቁ ይማራሉ፡፡ ብልሃቱ በማንበብ ሂደትና ድህረ ማንበብ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ለማብራራት (ለማጣራት)፣ ለማረጋገጥ እና ለማረም ይጠይቃሉ፡፡

ለ. መተባበር

ይህ የማንበብ ብልሃት ከሌሎች አቻዎች (ከአንድ ወይም ከብዙዎች) ጋር መስተጋብር መፍጠር የቋንቋ ችሎታን እና የምንባብ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል ነው፡፡ይህ ብልሃት ከቋንቋ መማር ብልሃት ጋር መሰረታዊ ግንኙነት ያለው ሲሆን ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸውን ለማጎልበት ብቻ ሳይሆን በራስ መተማመንን እና ማህበራዊ ተቀባይነትን እናዲያጎለብቱ ይረዳል፡፡

## 2.3. የማንበብ ትምህርት ዓላማ

ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ ለምን ዓላማ አስበው እንደሚያነቡት ለማሳወቅ የተለያዩ ምንባቦችን በማስነበብ ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ የንባብ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ ጥሩ የንባብ ችሎታ ያላቸውን አንባቢዎች ማፍራት ነው (Mei-Yun 1993)፡፡ Grant(1987:60) «መሰረታዊ የመረዳት ችሎታን በማሳደግ የምንባቡን አጠቃላይ ሀሳብ አንብቦ ለመረዳት፣ በማንበብ አጠቃላይ እውቀትን ለማሳደግ፣ የሚነበብበትን አላማ ለመወሰን፣ የንባብ ዘዴንም እንደ ሁኔታው ለመለወጥ እና ሂሳዊ የማንበብ ችሎታን ለማዳበር ያስችላል» በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ Williams (1990) አገላለፅ የንባብ ትምህርት ከቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ቋንቋውን የመለማመድ እድል እንዲያገኙ፣ ከሚያነቡት ነገር የሚፈልጉትን መረጃ ለይተው ማውጣት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም Nuttall (1996:21) «ንባብን ማስተማር ተማሪዎች የንባብን ልምድ እንዲኖራቸው ከማስቻሉም በላይ እንግዳ የሆነ ምንባብ ቢኖር እንኳን በአጋዥነት በተገቢው ፍጥነት፣ በጥሞና እና በበቂ ግንዛቤ እንዲያነቡ ያስችላቸዋል»፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በተመለከትነው አንፃር የንባብ ክሂል ትምህርት የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡፡

1. ተማሪዎች እንደየ ዓላማቸው እና እንደየ ጽሁፉ አይነት የተለያዩ ብልሀቶችን ተጠቅመው ማንበብ እንዲችሉ፣
2. አስተማማኝ የቋንቋ ብቃት እንዲኖራቸው፣
3. የተፃፉ ጉዳዮችን በተገቢው መንገድ እንዲረዱ፣
4. አንድ ፅሁፍ ወይም አረፍተ ነገር የተለያየ መልዕክት ሊኖረው እንደሚችል እንዲገነዘቡ ማስቻል ነው፡፡

## 2.4. የማንበብ ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከሚለመድ እና አይቀሬ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ንባብ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ንባብ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ስለ ንባብ አስፈላጊነት ተስፋዬ (1981፣60) «ማንበብ በተለይ በአሁኑ በሰለጠነው ዘመን አስፈላጊ ከሚባሉት መለያዎች ውስጥ የሚደመር ነው፡፡ ማንበብ ዕውቀት የማግኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን እንደ ዋና፣ ኳስ ጫወታ፣ ሽርሽር፣ እና እንደ አደን ሁሉ መዝናኛ ሆኗል፡፡» በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ Grellet (1981) አገላለፅ የንባብ አስፈላጊነትን ከሶስት ጥቅሞች አንጻር ማየት ይችላል፡፡ አንደኛ ደስታን ለማግኘት፣ ሁለተኛ ለሕይወት ወይም ለመኖር ሲባል ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ መማር ወይም እውቀት ለመሸመት ናቸው፡፡ ይህን ሁኔታ ከተማሪዎች የቋንቋ ክፍለ ጊዜ አንጻር ስንመለከተው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በዋናነት የሚያነቡት የንባብ ክሂላቸውን ለማሻሻል እና ዕውቀት ለማግኘት ነው፡፡ Harris (1990) ከዚህ በላይ የተገለጸውን የምሁሩን ሀሳብ በመጋራት ሶስት አይነት ዋና ዋና የንባብ ተግባራት እንዳሉ ያስረዳሉ፡፡ ተግባራቱም አገልግሎታዊ ተግባር፣ እድገታዊ ተግባር እና የመዝናኛ ተግባር ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የንባብን ትምህርት አስፈላጊነት McDonouph (1999) በሚከተለው ሁኔት ጠቅለል አድርገው ገልፀውታል፡፡

1ኛ. በጋዜጦች፣ በመፅሔቶች፣ በዘገባዎች የሚቀርቡትን ሀሳቦች ለመረዳት እና ለመዝናናት አልያም እራስን ለማስደሰት ይረዳል፡፡

2ኛ. ከዚህ በፊት የማናውቃቸውን ስለተለያዩ ርዕስ ጉዳዮች መረጃ ወይም ዕውቀት ለማግኘት ይረዳል፡፡

3ኛ.የሰው ልጅ ማህበራዊ ስለሆነ መረጃዎችን ይለዋውጣል፡፡ በመሆኑም ይህን የሚለዋውጠውን መረጃ ከሚያገኝበት ዘዴ መካከል ንባብ አንዱ ነው፡፡

4ኛ. በአለንበትም ሆነ በሌላ ቦታ እየተከናወኑ ያሉ ክንውኖችን ለማወቅ አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዎች መካከል አንዱ ነው ወዘተ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ንባብ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ የንባብ ብልሀቶችን ተጠቅመው የተለያዩ ይዘት ያላቸውን ንባቦች እንዲያነቡ ማድረጉ ብልሀቶችን ተጠቅመው በእውቀታቸው እንዲያበለፅጉ ከማድረግ በዘለለ ሊያዝናናቸው የሚችል በመሆኑ የንባብ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡

## 2.5. የአንብቦ መረዳት ብልሃት አይነቶች

የአንብቦ መረዳት ብልሀት በቁጥር እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ Armbruster and Osborne (2002) National Reading በመጥቀስ መስፈርት ያሟሉ ብልሀቶች ብለው ያሰፈሩት ማጠቃለል፣ ማዋሀድ፣ ምስል ፈጠራ፣ የማዛመድ እና መተንበይ ናቸው፡፡

### 2.5.1. ማጠቃለል

አንድ በዝርዝር ተለጥጦ የቀረበ ፅሁፍ በማንበብ ሃሳቡን በታመቀና በተመጠነ መልኩ ለማስፈር የሚያስችል የአንብቦ መረዳት ብልሀት ይባላል (Oxford 1990)፡፡ ይህ ብልሀት የመነሻ ፅሁፍ ይዘት ሳይለውጥ ዋና ዋና ሃሳቦችን ብቻ ለይቶ በማውጣት በቅርፅ ላይ ሰፊ ማሻሻያ ማድረግን ይፈላጋል፡፡

ማጠቃለል ከአንድ ፅሁፍ ጠቃሚ ሀሳቦችን ከመለየት ባሻገር ሀሳቦችን በተገባጠመና በሰመረ መልኩ የመፃፍ ችሎታን የሚጠይቅ እንደሆነ Norton (1997) ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ Anderson (1982) ማጠቃለልን ፅሁፍ ተኮር በሚል መክፈል የሚቻል መሆኑን ጠቁመው ተማሪዎች ፅሁፍ ተኮር ማጠቃለልን እንዲለማመዱ በማድረግ የፅሁፍ ችሎታ በማጎልበት ይልቅ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ እንዲያተኩሩ ማድረግ እንደሚሻል አስገንዝበዋል፡፡ አንባቢ ተኮር የማጠቃለያ አቀራረብ ስልት

ተማሪዎቹ ማጠቃለያውን ለሌላ አንባቢ በሚቀርብ መልኩ እንዲያዘጋጅ ስለሚጠብቅ ለፅሁፍ ርዝመት ለሰዋስው አወቃቀሩና ስለ ግጥምጥምነቱ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሀት የሆነውን ማጠቃለልን ከመረዳት ብልሀት ወደ መፃፍ ተግባርነቱ እንዲያመዝን የሚያደርጉት ይሆናል፡፡ ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ ጠቃሚና ዝርዝር ሀሳቦችን ጨምቆ ማውጣትን እንደሚጠይቅ የሚያስረዱት Armbruster and Osborne (2002)፤ ተማሪዎችን የማጠቃለል ብልሀትን ለማለማመድ በርካታ ቴክኒኮችን መጠቀም እንደሚቻል ጠቁመዋል፡፡ የመጀመሪያው ቴክኒክ የአንድን መልዕክት መዋቅር መሰረት ያደረጉ ቁልፍና የአጠቃላይነት ሀሳብን የሚያመለክቱ የቃላትና ሀረጋትን በማስፈር ተማሪዎቹ ፅሁፉን እያነበቡ በመሪ ቃላትና ሀረጋቱ ስር የሚካተቱ ሀሳቦችን እያዩ እንዲያሰፍሩ የሚከናወን ነው፡፡

ሌላው የማጠቃለል ብልሃትን ለመለማመድ የሚያስችል ቴክኒክ እርከናዊ እንደሆነ Taylor and Bachman (1984)ን በመጥቀስ Armbruster and Osborne (2002) ያስረዳሉ፡፡ ይህን ቴክኒክም ለመተግበር መነሻ ላይ ተማሪዎቹ ፅሁፉን እያነበቡ ርዕሶችን፤ ንዑስ ርዕሶች እና አንቀፆቹን መሰረት አድርገው ንድፍ ያዘጋጃሉ፡፡ በመቀጠልም በየርእሶቹ፤ በየንዑስ ርዕሶቹና በየአንቀፆቹ በውስጥ ያሉ ዋና ዋና ሀሳቦች ለይተው ያወጣሉ፡፡ በመጨረሻም በየደረጃው ያወጧቸውን ዋና ዋና ሀሳቦች መሰረት በማድረግ አንድ መሪ ሃሳብን በማፍለቅና ዋና ዋና ሀሳቦችን በመሪው ሀሳብ ስር በማስተሳሰር የምንባቡን ጠቅላላ ሀሳብ ይገልፃሉ፡፡

### 2.5.2.ማዋሀድ

በከፍተኛ ደረጃ አንብቦ ከመረዳት ክህሎች ውስጥ አንዱ ማዋሀድ ነው፡፡ በንባብ ትምህርት ማዋሀድ ተማሪዎች በሚያነቡት ፅሁፍ ውስጥ የቀረቡ ፅንሰ ሀሳቦችን፣ ጠቃሚ ዝርዝርና ዋና ዋና ሀሳቦችን በመጭመቅና እነዚህን ሀሳቦችን የሆነ ቅርፅ በማስያዝ አደራጅቶ የማቅረብ ክሂልን የማዳበር ሂደት ነው፡፡ ተማሪዎች በሚያነቡት ፅሁፍ ወስጥ ያሉ ሀሳቦችን የሆነ ቅርፅ አስይዘው በሚያደራጁበት ጊዜም ከፍተኛ ደረጃ የሚባሉ የማሰብ ክህሎቻቸውን የግል ይጠቀማሉ፡፡

### 2.5.3. ማዛመድ

ይህ የብልሀት አይነት ንቁ ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያገኟቸውን ሀሳቦች/እውቀቶች ከራሳቸው ህይወትና ከዚህ ቀደም ካነበቧቸው ፅሁፎች ሀሳቦች ጋር ያገናዝቧቸዋል፡፡ ተማሪዎች ያነበቡትን ሁሉ ትክክል ነው ብለው የሚቀበሉ አይነት ሰዎች እንዳይሆኑ በሚያነቧቸው ጽሑፎች ውስጥ የሚያገኟቸውን ዕውቀቶች የመምረጥ፣ የመቀበልና የመቃወም ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያስችሏቸው መልመጃዎች እየሰሩ መለማመድ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.5.4. ምስል ፈጠራ

አንድ ፅሁፍ በስዕሎች፣ በካርቱኖች፣ በምስሎች፣ በሰንጠረዦች፣ በግራፎች፣ በካርታዎችና ፎቶዎች ተደግፎ ሲቀርብ ማየት የተለመደ ክስተት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ አንባቢ እንዲህ ያሉ ምስሎችን አንድምታ መረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በንባብ ትምህርትን ተማሪዎች የተለያዩ ካርቶኖችን፣ ስዕሎችን፣ ግራፎችን፣ ሰንጠረዦችን፣ ካርታዎችን፣ ተመልክተው የምስሎችን አንድምታ የመረዳት ክሂላቸውን የሚያዳብሩ መልመጃዎችን እየሰሩ መለማመድ ይኖርባቸዋል፤ ተግባራቱም በክፍልና በቤት ስራነት ሊሰጡ ይችላሉ (Nuttall 1996)::

### 2.5.5. መተንበይ

ትንበያ አንድ አንባቢ ከሚያነበው ፅሁፍ ጋር መስተጋብር (interaction) የሚፈጥርበት አንድ መንገድ ነው፡፡ትንበያ ማለትም አንድ አንባቢ ሊያነበው ያሰበው ፅሁፍ ወይም እያነበበው ያለው ፅሁፍ ቀጥሎ ምን ምን ጉዳዮችን ሊያነሳ እንደሚችል ማሰብ ወይም መገመት ነው፡፡ ትንበያ ማለት ለማንበብ የተመረጠውን ፅሁፍ ርዕስ በማየት ፅሁፉ ስለምን ሊገልፅ እንደሚችል፣ እንዲሁም የፅሁፉን የተወሰነ ክፍል በማንበብ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን እየገመቱ የማንበብ ሂደት ነው (Grellet& Nuttall, 1996)::

ስለዚሁ የመማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች በንባብ ትምህርት የተማሪዎችን የመተንበይ ክሂል ለማዳበር የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በአግባቡ ሊያካትቱ ይገባቸዋል፡፡

## 2.6. ጾታና አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች

William (1985) በማናቸውም የዕድሜ ደረጃ ሴት ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት፣ በቃላት ዕውቀት መጠን፣ በንባብ ክሂል ወዘተ. ከውንዶች የተሻሉ መሆናቸውን የሚያመለክቱ እንደሆኑ ይጠቅሳሉ፡፡ተመራማሪዎች እንደሚጠቁሙት ንባብን የሴቶች ተግባር እንደሆነ የመቁጠር አዝማሚያም በአብዛኛው የሚታይ ሲሆን፤(Betz& Fitzegerald 1987) የWilliams የጥናት ግኝት እንደሚያመለክተው ንባብን የሴቶች ተግባር አድርገው ከሚመለከቱት ይልቅ ይህን መሰሉ አመለካከት የሌላቸው ወንዶች የተሻለ የማንበብ ችሎታ ያላቸው መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ በአንፃሩም፤ በንባብ ክሂል ረገድ በወንዶችና ሴት ተማሪዎች መካከል ልዩነት የሌለ መሆኑን የሚጠቁሙ ተመራማሪዎች አሉ፡፡ በእስራኤል ሀገር በንባብ ረገድ ልዩነት ያለመታየቱን መግለፃቸውን እና ይህም ማኅበረሰቡ ለሴቶችና ለወንዶች ከሚሰጠው እኩል የሆነ ኃላፊነት ጋር ተዛምዶ ሊኖረው እንደሚችል Bank& Good (1980) ይጠቁማሉ፡፡

ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከጾታ አንፃር እንደ መሆኑም  ጥናቶች በሴቶችና በወንዶች መካከል በአንብቦ መረዳት ዙሪያ ሰፊ የጾታ ልዩነት አለ በማለት ያመለከቱት በፊላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ልዕለአእምሮዊ የማንበብ ብልሃት ትኩረትን የሳበ ጉዳይ ሆኖ ቀርቧል (Iwai 2011)፡፡ «ልዩነት አለ ይኸውም፤ የ15 ዓመት እድሜ ባላቸው ተማሪዎች ላይ የተደረገው የናሙና ጥናት እንደሚያስረዳው 60% የሚሆኑት ሴቶች ከወንዶቹ ይልቅ የተሰጣቸውን ምንባብን አንብቦ በመረዳት ዙሪያ የተሻለ ተሞክሮ እንዳላቸው ተረጋግጧል፡፡ የልዩነቱ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደውም ሴቶች ንባብን የሚያፈቅሩ ሆነው መገኘታቸውንና ለንባብ በቂ የሆነ ጊዜን መስጠት በመቻላቸው ነው» (Cromley 2005, 195-199)::

Peacock and Ho (2003) ቻይና ውስጥ ባደረጉት ጥናት ሁለተኛ ቋንቋን ከሚያጠኑ 1005 ተማሪዎች በወሰዱት ናሙና እንደገለፁት ሴቶች ስድስቱንም ዓይነት የማንበብ ብልሃቶች (በአጥኚዎቹ የተዘጋጁትን) ተጠቅመው ተገኝተዋል፡፡ Tindall and Arryo (2005) እንደሚሉት በሴቶችና በወንዶች መካከል በብልሃት አጠቃቀም ላይ የሚታየው ልዩነት ከባህላዊ መቼታቸው ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው፡፡ አስቀድመው ከነበሩት ጥናቶች በተቃራኒው አንዳንድ ጥናቶች በብልሃት አጠቃቀም ላይ በሴቶችና በወንዶች መካከል አንዳች ልዩነት የለም በማለት ያስረዳሉ፡፡ Abu (2003) ባደረጉት ጥናት በወንዶችና በሴቶች መካከል አንዳች ዓይነት ልዩነት እንደሌለ ያሥረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለፁት ጥናታዊ ፅሁፎች መረዳት የሚቻለው ማንበብን የመማር ብልሃቶችን አጠቃቀም በተመለከተ በተለያየ የውጪ ሀገር ጥናቶች ልዩነት እንዳለ እና እንደሌለ የተገለፀ ሲሆን፣ እርሱም በኢትዮጵያ አውድ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የማንበብ ብልሃት አጠቃቀም አውንታዊና አሉታዊ ሚና ምን እንደሚመስል ለጥናቱ በተመረጡት ማለትም የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ብልሃቶች አጠቃቀም ለመፈተሽ ይሞከራል፡፡

## 2.7. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የሚቃኙበት ነው፡፡ በመሆኑም ሶስት ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ በዳሰሳው ወቅት የጥናቱ ርዕስ ምንድን ነው፣ መቼና የት ተጠና፣ ዋና ዓላማ ምንድን ነው፣ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች ምን ምን ናቸው፣ ለማጥናት የተመረጠው ስነ ዘዴ ምንድን ነው፣ የተመረጠው ስነ ዘዴ ጥናቱን ለማጥናት ተገቢ ምርጫ ነው ወይስ አይደለም፣ በትንተናው ምን ምን ዋና ዋና ጉዳዮችን ዳሰሰ፣ ግኝቱስ ምንድን ነው፣ ምንስ የይሁንታ ሀሳብ አቀረበ የሚለው ይዳሰሳል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር በምን እንደሚመሳሰል እና እንደሚለያይ የሚያሳይ ይሆናል፡፡

ተክላይ (2000) "በትግረኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ እና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ንባብ ጊዜ የንባብ ብልሃት አጠቃቀም እና የመምህራን ግንዛቤ ተጣጥሞ ፍተሻ - በአክሱም ከተማ አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መነሻነት" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ፣ በአማርኛ ቋንቋ ችሎታቸው በከፍተኛ፣ በመካከለኛ እና በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ተተኳሪ ተማሪዎች፣ ከንባብ ብልሃት አጠቃቀማቸው ጋር ተጣጥሞ ያለው መሆን አለመሆኑን መመርመርን እና የአማርኛ መምህራኑ የንባብ ብልሃት ግንዛቤም ከተማሪዎቹ የንባብ ብልሃት አጠቃቀም ጋር ተጣጥሞ ያለው መሆን አለመሆኑን መፈተሽ ነው፡፡ አጥኚው ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ወደ ተመረጡት የክፍል ደረጃዎች በምልከታ፣ በፅሁፍ መጠይቅ እና በቃለ መጠይቅ መረጃ ከሰበሰበ በኋላ ተተኳሪ ተማሪዎቹ በምልከታ የተጠቀሙባቸውን የንባብ ብልሃት አጠቃቀሞች በፅሁፍ መጤቅና በቃል መጠይቅ ከተጠቀሙባቸው የንባብ ብልሃት አጠቃቀሞች ጋር ለመማሰካከር ተሞክሯል፡፡

የተክላይ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስልበት እና የሚለይበት ሁኔታ አለ፡፡ የአጥኚው ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱቹም በንባብ ላይ በመሆኑ እና የብልሃት አጠቃቀማቸውን በመመልከታቸው ነው፡፡ ከአጥኚው ጥናት ጋር የሚለያይበት ሁኔታ ደግሞ የአጥኚው ጥናት የንባብ ብልሃት ሆኖ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን የሚመለከት ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ የአንብቦ መረዳት ብልሃት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን የሚመለከት በመሆኑ እና እንደ ዋነኛ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀመው ምልከታ በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

አፈወርቅ (2008) "በጋሞ ጎፋ ዞን በምዕራብ አባያ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፈፊትና ኢ አፈፊት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው ቃላት የመማር ብልሃቶች ትንተና" የጥናቱ ዓላማ የአፈፊትና ኢአፈፊት ተማሪዎች ቃላትን ለመማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች መተንተን ነው፡፡ ለዓላማው መሳካት በፅሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የአጥኚው ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በብልሃቶች ላይ በመሆኑ እና ሁለቱቹም የተጠቀሙት የመረጃ መሳሪያ መንገዶች የፅሁፍ መጠይቅና የቃል መጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡

የአጥኚው ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚለያይበት ደግሞ አጥኚው ጥናት አፈፊትና ኢአፈፊት የሆኑ ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ሲማሩ የሚጠቀሙባቸው እንዲሁም የክፍል ደረጃው ሁለተኛ ደረጃ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆን የኔ ጥናት ደግሞ የአንብቦ መረዳት የአንደኛ ደረጃ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆኑ ከጥናቴ የሚለይ ነው፡፡

ሠርካለም (2010) አእምሮኣዊ እና ልዕለ አእምሮኣዊ  የማንበብ ብልሃት አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያላቸው አስተዋፅኦ የሚል ሲሆን አጠቃላይ የጥናቱ ምዕራፍ አምስት ሲሆን ጥናቱ መጠናዊ ና ዓይነታዊ የምርምር አይነቶችን የተከተለ ነው፡፡ በዋናነት መጠናዊ ተግባራዊ ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደበት የመረጃ መሳሪያ በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ ነው፡፡

የአጥኚዋ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁኔታ አለ ሁለቶቹም የአንብቦ መረዳት ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ከአንብቦ መረዳት ብልሃት ውስጥ በሁለቶቹ ላይ ማለትም በአእምሮአዊ ና ልዕለ አእምሮአዊ ብልሃት ላይ በመስራቷ እና በጥናቱ ላይ ከፆታ አንፃር በመመልከቷ ነው፡፡

የአጥኚዋ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚለያይበት ደግሞ ከአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ውስጥ አጥኚዋ በሁለቶቹ ላይ በመመስረቷ እና የኔ ጥናት ደግሞ አምስቶቹን የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መሰረት ያደረገ እንዲሁም አጥኚዋ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመሆኑ እና መጠናዊ የመረጃ አተናተንን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቿ ፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ በመሆኑ ከኔ ጥናት የሚለይ ነው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የቀደሙት ጥናቶች ለተመራማሪዋ የጥናቱን አሰራር ለመንደፍ የተመራማሪዋን የትምህርት ዳራ ሲያበለፅጉ እንደ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች ይዘት ትንተና ለመገንባት እና የጥናቱን ውጤቶች ለመተርጎም የሚረዱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአጠናን ዘዴዎች የናሙና አመራረጥ ዘዴ፣እንደዚሁም የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ይካተታሉ።

### 3.1. የአጠናን ዘዴ

የጥናቱ አብይ ትኩረት የተጠኝዎችን የአንብቦ መረዳት ብልሃት ከፆታ አንፃር መፈተሽ ነው። ጥናቱ በዋናነት ገላጭ ነው። ጥናቱ ገላጭ የሆነበት ምክንያትም አብዛኛዎቹ መረጃዎች ተሰብስበው የሚተነተኑት በገለፃና ማብራሪያ ስልትን ስለሚጠቀም ነው። ገላጭ ምርምር ዘዴዎች ሁኔታዎች በተፈጥሮ ሲከሰቱ ለማጥናት የሚረዱ እና ዝርዝር ማብራሪያዎች ስለ ተሳታፊዎች አውድ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ይሰጣሉ (Maxwell 2012)። ገላጭ ምርምር/ ጥናት በምን፣ እንዴት እና ለምን ለሚጀምሩ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ይረዳል (Green & Thorogood, 2014, 5-25)

### 3.2. የናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ በጋራ ጉሪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል። ለዚህም ምክንያቱ ጥናቱን ለማካሄድ መረጃ ለማግኘት አጥኚዋ በዚያው ትምህርት ቤት የምታስተምር ከመሆኗ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ስላልሆነ ነው። ጥናቱ ከክፍል ደረጃና ከተማሪዎች አንፃር የክፍል ደረጃው በአላማ ናሙና፤ እንዲሁም በዓላማ ተኮር ናሙና የሚመረጡ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ነው። በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ወንድ 99፣ ሴት 96 በጥቅሉ 195 ተማሪዎች በዓላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል። አላማ ተኮር የሆነበት ምክንያት ኢ አፈፊት ተማሪዎችን ብቻ መርጦ ስለ ወሰደ ነው። የሰባተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ መምህራን ደግሞ ሁለት ናቸው።ሁለቱን መምህራን ደግሞ በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ተወስደው በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል። ይህም የሆነው ያለው (1998) እንደገለፁት እና ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ተመራማሪው ያገኛቸውን ሁሉንም የጥናቱን አካላይ አካላት በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ አድርጎ ሲወስድ ጠቅላይ ንሞና ይባላል።

በተጨማሪም በዚህ ትምህርት ቤት በጥቅሉ ከሚገኙ ተማሪዎች በመረጃ ሰጭነት ለማካተት ከጊዜ፣ ከመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት እንዲሁም ከትንተና አንፃር አስቸጋሪ ስለሚሆን በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ወንድ 46(23.6%)፣ ሴት 44(22.56%) ከሁለቱም ፆታ በድምሩ 90(46.15%) ተማሪዎች ብቻ በጥናቱ እንዲካተቱ ቢደረግም ወንድ 5(2.63%) ሴት 4(2.10%) ድምር 9(4.61%) የሚሆኑ ተማሪዎች በተለያየ ምክንያት መጠይቁን ሳይሞሉ ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም ጥናቱን በትክክል የሞሉ ተማሪዎች ወንድ 41(50.61%) ሴት 40(49.4%) ድምር 81(41%) ናቸው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት መሳካት ግብ መቼ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተጠኚ ተማሪዎች የሚሰሩ የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.3.1.የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ ዋናው የመረጃ መሰብሰብያ መሣሪያ ሲሆን፣ አላማውም የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በተማሪዎች መካከል ልዩነት ማምጣት አለማምጣቱን ለመፈተሽ ያለመ ነው፡፡ የጽሁፍ መጠይቆቹ ከዚህ ቀደም በሃገርም ሆነ ከሃገር ውጪ የተሰሩ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም መሰረት በማድረግ ለጥናቱ በሚያመች መንገድ የተዘጋጁ ናቸው፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ ተዘጋጅቶ የቀረበው ለተጠኚ ተማሪዎች ሲሆን፤ መረጃው በጽሁፍ መጠይቅ እንዲሰበሰብ የሚፈለግበት ምክንያትም ማንነታቸው ሳይገለፅ ስለሚፅፉ ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት ስለሚያስችል ነው፡፡ የጥያቄዎቹ ይዘትም በአንብቦ መረዳት ብልሃቶች የተሻሉት እነማን እንደሆኑ፤ የአንብቦ መረዳት በልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር ምን እንደሚመስል፤ ለመፈተሽ ያለሙ ናቸው፡፡ የመጠይቁ ጠቀሜታ ብዛት ያላቸው መላሾች በቀረበው ጥያቄ መሰረት የፈለጉትን ጥያቄ መሰረት የፈለጉትን ጥያቄ መስማማት አለመስማማታቸውን ለማመልከት (አቋም ለመያዝ) የሚችሉበት መሆኑ ነው፡፡ አጥኚዋ ብዙ ሰዎች የሰጡትን ምላሽ አንፃራዊ በሆነ መልኩ በቀላሉ (በተመቸ ሁኔታ) ለመተንተን ያስችላታል፡፡ በዚህ ጥናት የፅሁፍ መጠይቁ አምስት አማራጮች አሉት፡፡ እነሱም (1 በፍፁም አልጠቀምም፣ 2 አልፎ አልፎ (ውስን ጊዜ) እጠቀማለሁ፣ 3 አንድ አንድ ጊዜ እጠቀማለሁ

የመጠይቁ አቀራረብ እያንዳንዱ የማንበብ ብልሃት በስድስት ጥያቄዎች እንዲተካ የተደረገ ሲሆን የፅሁፍ መጠይቁ 30 አሳሽ የፅሁፍ ጥያቄዎችን ያካተተ ነው፡፡ ከአእምሮታዊ የማንበብ ብልሃት 6፣ ከልፅለ አእምሮታዊ 6፣ ከትውስታ 6፣ ከማካካስ 6 እና ከማህበራዊ የማንበብ ብልሃት 6 ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ የፅሁፍ መጠይቁን ዝርዝር ጥያቄዎች ከአባሪ አንድ ይመልከቱ፡፡

### 3.3.2. ቃለ መጠይቅ

በዚህ ቃለ መጠይቅ በጠቅላላው ሁለት መምህራን እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ ቃለ መጠይቁ ተዘጋጅቶ የቀረበው በናሙናነት በፅሁፍ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማመሳከር ለመፈተሽና ተጨማሪ መረጃዎች ካሉም ለማግኘት ነው፡፡ መረጃው በቃለ መጠይቅ እንዲሠበሠብ የሚፈለግበት ምክንያት በፅሁፍ መጠይቁ የቀረበውን መረጃ ለማጠናከር ነው፡፡ የጥያቄዎቹ ይዘትም ተማሪዎች ስለአንብቦ መረዳት ብልሀቶች አጠቃቀም ያላቸውን የቀደመ እውቀት፣ የአንብቦ መረዳት ብልሃት ምርጫቸውንና ውጤታማነታቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ያለሙ ናቸው፡፡

## 3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የፅሁፍ መጠይቆችን በመስጠት የተገኘው አሀዛዊ መረጃ በመቶኛ ስሌት የምርምር ዘዴ አይነት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የተሰላው አሀዛዊ መረጃ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል መልኩ በገላጭ ምርምር አቀራረብ ዘዴ በዝርዝር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በጥናቱ በነፃ ማሰብ ያሠቡትን ማንፀባረቅ እና ያሠቡትን ነገር አስታውሶ የመናገር ቃለመጠይቅ የተገኘውን መረጃ አሀዛዊ መልክ እንዲይዝ በማደረግ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡በተለያዩ መንገድ የተሰበሰበው መረጃ ለአተናተን እንዲያመች በጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ በተንፀባረቁት ዓላማ መሰረት ትንተናው ቀርቧል፡፡ የጥናቱ ዓላማም ፦ ተማሪዎች የበለጠ የሚጠቀሙት የትኛውን ብልሃት እንደሆነ መለየትና በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም መኖር አለመኖሩን መለየት የሚሉ ናቸው፡፡

ከአንብቦ መረዳት ንዑስ ብልሃቶች ውስጥ ተማሪዎች የበለጠ የሚጠቀሙት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ በመቶኛ ተሰልቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም ከሞሉት የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በአፅማሯዊ፣የትውስታ፣አካካሽ፣ ልዕለ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ በሚሉ አምስት ንዑስ ክፍሎች ተመድበዋል፡፡ ተማሪዎቹ ለየንዑስ ብልሃቶቹ ያገኙት ውጤት በመቶኛ ተሰልቶ ተፈትሿል፡፡

ከዚህም ሌላ በጥናቱ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማወቅ ከዋለው የፅሁፍ መጠይቅ በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተግባሪያዊ ተደርጓል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## መረጃ ትንተና

በዚህ የመረጃ ትንተና ክፍል አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም ከፆታ አንፃር በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ጋራ ጉሪ የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት በሚመለከት በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ከዓላማዎቹ አንፃር ቀጥተኛ ብልሃቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች መጀመሪያ ላይ፣ ቀጥሎ ደግሞ ኢ-ቀጥተኛ ብልሃቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ በያንዳንዳቸው ንዑሳን ብልሃቶች ስር በሚገኙ ዝርዝር ብልሃቶች መረጃ ተማሪዎች የበለጠ የሚጠቀሙት የትኞቹን የአንብቦ መረዳት ብልሃት እንደሆነ መለየት፣ በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም መኖር አለመኖሩን የሚያሳይ ትንተና ቀጥሎ በቅደምተከተል ቀርበዋል፡፡

### 4.1. ቀጥተኛ ብልሃቶች

አንብቦ የመረዳት ብልሃት ለመማር ተገቢ የሆኑ ቀጥተኛ ብልሃቶችም አእምሯዊ፣ ትውስታና አካካሽ ብልሃቶች በሚባሉ ሶስት ንዑሳን ምድቦች የሚከፋፈሉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚያመለክተው የተማሪዎች ቀጥተኛ የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው በተመጣጣኝ ደረጃ መጠቀማቸው ተረጋግጧል፡፡ በሶስቱ ንዑሳን ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ብልሃቶች መረጃ እንዲሰጡ 18 በፅሁፍ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ቀርቦላቸዋል፡፡ እያንዳንዳቸው የቀጥተኛ ንዑሳን የመማር ብልሃቶች ስድስት ስድስት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹም 1-6 አእምሯዊ 7-12 ትውስታ እና 13-18 አካካሽ ቢሆኑም አጠቃላይ ለተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ የተሰጠው ጥያቄ ብዛት 30 ሲሆን 60% የቀጥተኛ የመማር ብልሃት ነው (የእያንዳንዱን ጥያቄዎች ዝርዝር ከአባሪ አንድ ይመልከቱ)፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄዎች ስር አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡በቀረቡት ጥያቄዎች 1. በፍፁም አልጠቀምም 2. አልፎ አልፎ 3. አንዳንድ ጊዜ 4. አብዛኛውን ጊዜና 5. ሁልጊዜ ሲሆኑ የመለሱትን የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ እያንዳንዱ ንዑሳን ብልሃቶች በጥናቱ ዓላማ መሰረት ተተንትኗል፡፡

#### 4.1.1.አእምሯዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሃቶች የሚመለከቱ መልስ እንዲሰጡ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ተማሪዎች የመለሱት ምላሾች በቁጥር (ዝርዝሩን ከአባሪ ሰባት ይመልከቱ) በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ስድስት አእምሯዊ ብልሃቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

**ሠንጠረዥ 1. አእምሯዊ ብልሃቶች መረጃ**

| ተቁ | ብልሃቶች | አምራጮች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | | | አብዛኛውን ጊዜ | | | | አንዳንድ ጊዜ | | | | አልፎ አልፎ | | | | በፍፁም አልጠቀምም | | | |
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. | ከማንበቤ በፊት ዕሁፉን በመመልከት ዕሁፉ ስለ ምን እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ | 4 | 9.75 | 3 | 7.5 | 19 | 46.34 | 14 | 35 | 8 | 19.51 | 10 | 25 | 10 | 24.39 | 9 | 22.5 | 0 | 0 | 4 | 10 |
| 2. | አጠቃላይ ዋና ሐሳቡን ለማግኘት በንባብ ሂደት ገረፍ ገረፍ በማድረግ አነባለሁ፡፡ | 5 | 12.59 | 10 | 25 | 10 | 24.39 | 4 | 10 | 4 | 10 | 9 | 22.5 | 7 | 17.07 | 8 | 20 | 7 | 17.07 | 8 | 20 |
| 3. | ምንባቡን በደንብ ካነበብኩኝ በኋላ ጥያቄዎችን በመስራት እለማመዳለሁ | 12 | 29.26 | 6 | 15 | 19 | 46.34 | 14 | 35 | 3 | 7.31 | 7 | 17.5 | 5 | 12.9 | 7 | 17.5 | 2 | 4.87 | 6 | 14.63 |
| 4. | ምንባቡን ከማንበቤ በፊት የዕሁፍን ርዕስ በማየት ከቀድሞ እውቀቴ ጋር አገኛለሁ፡፡ | 10 | 24.39 | 9 | 22.5 | 9 | 21.95 | 9 | 22.5 | 6 | 14.63 | 7 | 17.5 | 11 | 26.82 | 7 | 17.5 | 5 | 12.59 | 8 | 20 |
| 5. | በዕሁፍ ውስጥ ያሉ ክስተቶችን በቀላሉ ለመያዝና ረጅም ጊዜ | 8 | 19.51 | 11 | 27.5 | 14 | 34.14 | 12 | 30 | 9 | 21.95 | 5 | 12.5 | 7 | 17.05 | 9 | 22.5 | 3 | 7.31 | 3 | 7.5 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ትውስታ ለመፍጠር በአእምሮዬ ውስጥ ምስል እፈጥራለው፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6. | ከቀረበ አንድ ፅሁፍ በማነበበት ወቅት በምንባቡ ውስጥ ያለውን ዝርዝር እና ጠቃሚ ፊልፍዬ(ፊልጌ) ጥረት አደርጋለሁ፡፡ | 10 | 24.39 | 10 | 25 | 15 | 36.58 | 8 | 20 | 4 | 9.75 | 13 | 32.5 | 9 | 21.95 | 7 | 17.5 | 3 | 7.31 | 2 | 5 |
| | | 49 | 19.91 | 49 | 20.4 | 86 | 35.8 | 61 | 25.41 | 45 | 18.29 | 51 | 21.25 | 46 | 18.69 | 48 | 20 | 20 | 8.13 | 31 | 12.91 |
| አጠቃላይ ወንድና ሴት | | 98 | | 20.16% | | 147 | | 30.24% | | 96 | | 19.75 % | | 94 | | 19.34 % | | 51 | | 10.49% | |

ከላይ በሠንጠረዥ 1 እንደ ተመለከትነው ተጠኚዎች የፅሁፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ስድስት ዝርዝር ብልሃቶችን የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ምላሾች ተካፍሎ በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

ጥያቄ 1 ከማንበቤ በፊት ፅሁፉን በመመልከት ፅሁፉ ስለ ምን እንደሆነ እገምታለሁ የሚለውን ወንድ 4(9.75%)ና ሴት 3(7.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 19(46.34%) ሴት14(35%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 8(19.51%) ሴት 10(25%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 10(24.39%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ የማይጠቀሙ ሴት 4(10%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 2 አጠቃላይ ዋና ሐሳቡን ለማግኘት በንባብ ሂደት ገረፍ ገረፍ በማድረግ አነባለሁ የሚለውን ወንድ 5(12.59%)ና ሴት 10(25%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት4(10%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 15(36.58%) ሴት 9(22.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 4(10%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ የማይጠቀሙ ሴት 4(10%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 3 ማንባቡን በደንብ ከነበብኩኝ በኋላ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመስራት እለማመዳለሁ የሚለውን ወንድ 4(9.75%)ና ሴት 3(7.5)% የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 19(46.34%) ሴት14(35%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 8(19.51%) ሴት 10(25%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 4(10%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 7(17.07) ሴት 8(20%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 4 ምንባቡን ከማንበቤ በፊት የፅሁፉን ርዕስ በማየት ከቀድሞ እውቀቴ ጋር አገናኛለሁ የሚለውን ወንድ 9(29.26%)ና ሴት 6(15%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 19(46.34%) ሴት14(35%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 3(7.31%) ሴት 7(17.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 5(12.19%) ሴት 7(17.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 2(4.87) ሴት 6(14.63%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው በሁለቱ ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 5 በፅሁፉ ውስጥ ያሉ ክስተቶችን በቀላሉ ለመያዝና የረጅም ጊዜ ትውስታ ለመፍጠር በአእማሮዬ ውስጥ ምስል እፈጥራለሁ የሚለውን ወንድ 8(19.51%)ና ሴት 11(27.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 14(34.14%) ሴት12(30%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 9(21.95%) ሴት 5(12.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 7(17.07%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 3(7.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 6 ከቀረበ አንድ ፅሁፍ በማነብበት ወቅት በምንባቡ ውስጥ ያለውን ዝርዝር እና ጠቃሚ መረጃ ፈልፍዬ (ፈልጌ) ለማግኘት ጥረት አደርጋለሁ  የሚለውን ወንድ 10(24.39%)ና ሴት 10(25%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 15(34.14%) ሴት12(30%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 4(9.75%) ሴት 5(12.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 9(21.95%) ሴት 7(17.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 2(5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው በሁለቱ ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በአእምሯዊ ብልሃት በፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ንዑስ የአንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ ለ(6) ጥያቄዎች ብዛት ናሙና ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 49(19.91%) አብዛኛውን ጊዜ 86(35.8%)አንዳንድ ጊዜ 45(18.29%) አልፎ አልፎ 46(18.69%) በፍፁም

አልጠቀምም 20(8.13%) ሲሆን የሴቶች ናሙና 40(49.4%) ሁልጊዜ 49(20.4%) አብዛኛውን ጊዜ 61(25.45%) አንዳንድ ጊዜ 51(21.25%) አልፎ አልፎ 48(20%) በፍፁም አልጠቀምም 31(12.91%) የሁለቱ ፆታ ድምር ናሙና 81(46%) ሁልጊዜ 98(20.16%) አብዛኛውን ጊዜ 147(30.24%)አንዳንድ ጊዜ 96(19.75%) አልፎ አልፎ 94(19.34%) በፍፁም አልጠቀምም 51(10.49%) ውጤት የተገኘ ሲሆን በወንዶችና ሴቶች መካከል ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ  አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት የታየ መሆኑን ይገልፃል፡፡

### 4.1.2. የትውስታ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሃቶች የሚመለከቱ መልስ እንዲሰጡ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ተማሪዎች የመለሱት ምላሾች በቁጥር (ዝርዝሩን ከአባሪ ሰባት ይመልከቱ) በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ስድስት የትውስታ ብልሃቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

## ሠንጠረዥ 2. የትውስታ ብልሃቶች መረጃ

| ተቁ | ብልሃቶች | አምራጮች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | | | አብዛኛውን ጊዜ | | | | አንዳንድ ጊዜ | | | | አልፎ አልፎ | | | | በፍፁም አልጠቀምም | | | |
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. | የማነበውን ለማስታወስ እንድችል በጽሁፍ ውስጥ ያሉት ክስተቶች በአእምሮዬ ውስጥ ምስል እንዲፈጥሩ ለማድረግ እጥራለሁ፡፡ | 10 | 24.39 | 9 | 22.5 | 13 | 31.70 | 15 | 37.5 | 9 | 21.95 | 6 | 15 | 4 | 9.75 | 9 | 22.5 | 5 | 12.19 | 1 | 2.5 |
| 2. | አዳዲስ የአማርኛ ቋንቋ ሀሳቦችን | 4 | 24.39 | 6 | 15 | 13 | 31.70 | 8 | 20 | 9 | 21.95 | 8 | 20 | 7 | 17.07 | 10 | 25 | 8 | 19.51 | 8 | 20 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከማስታውስባቸው መንገዶች አንዱ ለእያንዳንዱ ሀሳብ በአእምሮዬ ውስጥ የራሱ ቅርፅ በመስጠት ነው። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 3. | አንድን ፅንሰ ሀሳብ ለማስታወስ ሀሳቡ የሚገኝበትን ቦታ፣ገፅ፣ሰሌዳ እና ሌሎች ምስሎችን እጠቀማለሁ። | 7 | 17.07 | 9 | 22.5 | 17 | 41.46 | 13 | 32.5 | 9 | 21.95 | 6 | 15 | 4 | 9.75 | 4 | 10 | 4 | 9.75 | 8 | 20 |
| 4. | የአማርኛ ስራዎችን መከለሴ ለማስታወስ ይረዳኛል። | 10 | 24.39 | 11 | 27.5 | 20 | 48.78 | 14 | 35 | 3 | 7.31 | 6 | 15 | 5 | 12.19 | 6 | 15 | 3 | 7.31 | 3 | 7.5 |
| 5. | የጽሁፉን አጠቃላይ ገፅታ ለመረዳት የፅሁፉን ይዘት እና ቅርፅ በአእምሮዬ ምስል እንዲፈጥር አደርጋለሁ። | 6 | 14.63 | 12 | 30 | 18 | 43.9 | 7 | 17.5 | 4 | 9.75 | 8 | 20 | 9 | 21.95 | 8 | 20.5 | 4 | 9.75 | 5 | 12.5 |
| 6. | የጽሁፉን አጠቃላይ ገፅታ ለመረዳት የፅሁፉን ይዘት እና ቅርፅ በአእምሮዬ ምስል እንዲፈጥር አደርጋለሁ። | 9 | 21.95 | 10 | 25 | 5 | 12.19 | 5 | 12.5 | 11 | 26.82 | 8 | 20 | 13 | 31.7 | 9 | 22.5 | 3 | 7.31 | 8 | 20 |
| | | 46 | 18.69 | 57 | 23.75 | 86 | 34.95 | 62 | 25.83 | 45 | 18.29 | 42 | 10.5 | 42 | 17.07 | 46 | 19.16 | 27 | 10.97 | 33 | 13.75 |
| አጠቃላይ ወንድና ሴት | | 103 | | 21.19% | | 148 | | 30.45% | | 87 | | 17.9% | | 88 | | 18.1% | | 60 | | 12.34% | |

ከላይ በሠንጠረዥ 2 እንደ ተመለከትነው ተጠኚዎች የፅሁፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ስድስት ዝርዝር ብልሃቶችን የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ምላሾች ተካፍሎ በመቶኛ ተተንትኗል።

ጥያቄ 7 የማነበውን ለማስታወስ እንድችል በጽሁፍ ውስጥ ያሉት ክስተቶች በአእምሮዬ ውስጥ ምስል እንዲፈጥሩ ለማድረግ እጥራለሁ የሚለውን ወንድ 10(24.39%)ና ሴት 9(22.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 13(31.70%) ሴት15(37.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 9(21.95%) ሴት 6(15%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 4(9.75%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 5(12.19%) ሴት 1(2.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 8 አዳዲስ የአማርኛ ቋንቋ ሀሳቦችን ከማስታውስባቸው መንገዶች አንዱ ለእያንዳንዱ ሀሳብ በአእምሮዬ ውስጥ የራሱ ቅርፅ በመስጠት ነው የሚለውን ወንድ 4(9.75%)ና ሴት 6(15%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 13(31.70%) ሴት8(20%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 9(21.95%) ሴት 8(20%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 7(17.07%) ሴት 10(25%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 8(19.51 ሴት 8(20%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 9 አንድን ፅንሰ ሀሳብ ለማስታወስ ሀሳቡ የሚገኝበትን ቦታ፣ገፅ፣ስሌዳ እና ሌሎች ምስሎችን እጠቀማለሁ የሚለውን ወንድ 7(17.07%)ና ሴት 9(22.5)% የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 17(41.46%) ሴት13(32%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 9(21.95%) ሴት 6(15%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 4(10%) ሴት 4(10%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 4(9.75) ሴት 8(20%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 10 የአማርኛ ስራዎችን መከለሴ ለማስታወስ ይረዳኛል የሚለውን ወንድ 10(24.39%)ና ሴት 11(27.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 20(48.78%) ሴት14(35%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 3(7.31%) ሴት 6(15%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 5(12.19%) ሴት 6(15%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 3(7.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 11 የጽሁፉን አጠቃላይ ገፅታ ለመረዳት የፅሁፉን ይዘት እና ቅርፅ በአእምሮዬ ምስል እንዲፈጥር አደርጋለሁ የሚለውን ወንድ 6(14.63%)ና ሴት 12(30.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች

ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 18(43.90%) ሴት 7(17.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 4(9.75%) ሴት 8(20%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 9(21.95%) ሴት 8(20%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 4(9.75) ሴት 5(12.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 12 የጽሁፉን አጠቃላይ ገፅታ ለመረዳት የፅሁፉን ይዘት እና ቅርፅ በአእምሮዬ ምስል እንዲፈጥር አደርጋለሁ የሚለውን ወንድ 9(21.95%)ና ሴት 10(25%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 5(12.19%) ሴት5(12.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 11(26.82%) ሴት 8(20%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 13(31.70%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 8(20%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በትውስታ ብልሃት በፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ንዑስ የአንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ ለ(6) ጥያቄዎች ብዛት ናሙና ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 46(18.69%) አብዛኛውን ጊዜ 86(34.95%)አንዳንድ ጊዜ 45(18.29%) አልፎ አልፎ 42(17.07%) በፍፁም አልጠቀምም 27(10.97%) ሲሆን የሴቶች ናሙና 40(49.4%) ሁልጊዜ 57(23.75%) አብዛኛውን ጊዜ 62(25.83%) አንዳንድ ጊዜ 42(10.5%) አልፎ አልፎ 46(19.16%) በፍፁም አልጠቀምም 33(13.75%) የሁለቱ ፆታ ድምር ናሙና 81(46%) ሁልጊዜ 103(21.19%) አብዛኛውን ጊዜ 148(30.45%)አንዳንድ ጊዜ 87(17.90%) አልፎ አልፎ 88(18.10%) በፍፁም አልጠቀምም 60(12.34%) ውጤት የተገኘ ሲሆን በወንዶችና ሴቶች መካከል ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ሁልጊዜና አብዛኛውን ጊዜ አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት የታየ ሲሆን በሌሎች ተቀራራቢነት አላቸው፡፡

### 4.1.3. የአካካሽ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሃቶች የሚመለከቱ መልስ እንዲሰጡ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ተማሪዎች የመለሱት ምላሾች በቁጥር (ዝርዝሩን ከአባሪ ሰባት ይመልከቱ) በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ስድስት አካካሽ ብልሃቶች ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

## ሠንጠረዥ 3. አካካሽ ብልሃቶች መረጃ

| ተቁ | ብልሃቶች | አምራጮች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | | | አብዛኛውን ጊዜ | | | | አንዳንድ ጊዜ | | | | አልፎ አልፎ | | | | በፍፁም አልጠቀምም | | | |
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. | በማነብበት ወቅት የፅሁፍ ይዘት መገመት ፣የፅሁፉን አወቃቀር መመልከት፣ነባር አጠቃላይእውቀትን መጠቀምና ግንኙነት መመስረት የመሳሰሉ ክንውኖችን አካሄዳለሁ፡፡ | 10 | 24.39 | 4 | 10 | 11 | 26.82 | 8 | 20 | 8 | 19.51 | 12 | 30 | 9 | 21.95 | 10 | 25 | 3 | 7.31 | 6 | 15 |
| 2. | በማነበው ፅሁፍ ውስጥ ያለውን የሀሳብ ትስስር እለያለው፡፡ | 8 | 19.51 | 9 | 22.5 | 15 | 36.58 | 9 | 22.5 | 10 | 24.39 | 7 | 17.5 | 6 | 14.63 | 12 | 30 | 2 | 4.87 | 6 | 15 |
| 3. | በማነበው ፅሁፍ ውስጥ የማገኛቸው ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀራጋት የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት ያግዙኛል፡፡ | 15 | 36.58 | 12 | 30 | 12 | 29.26 | 8 | 20 | 6 | 14.63 | 10 | 25 | 6 | 14.63 | 4 | 10 | 2 | 4.87 | 6 | 15 |
| 4. | በማነብበት ወቅት በፅሁፍ ውስጥ በቀረበው መረጃ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ ያለኝን ዳራዊ ዕውቀትና የግል ልምድ ለማዛመድ እሞክራለሁ፡፡ | 11 | 26.82 | 2 | 5 | 12 | 29.26 | 5 | 12.5 | 5 | 12.19 | 10 | 25 | 9 | 21.95 | 8 | 20 | 4 | 9.75 | 15 | 37.5 |
| 5. | በማነብበት ወቅት በተለያዩ የፅሁፉ አንጓዎች መካከል | 3 | 7.31 | 4 | 10 | 10 | 24.39 | 8 | 20 | 18 | 43.9 | 5 | 12.5 | 7 | 17.07 | 13 | 32.5 | 3 | 7.31 | 10 | 25 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቀረቡ ሀሳቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ለመለየት ጥረት አደርጋለሁ። | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6. | በማንበብ ሂደት ከመረጃዎች በመነሳት የመወሰን ብልሃትን በመተግበር በመስመሮች መካከል ለማንበብ ጥረት አደርጋለሁ። | 8 | 19.51 | 5 | 12.5 | 10 | 24.39 | 6 | 15 | 13 | 31.7 | 16 | 40 | 7 | 17.07 | 6 | 15 | 3 | 7.31 | 4 | 10 |
| | | 55 | 22.35 | 36 | 15 | 70 | 24.45 | 44 | 18.33 | 60 | 24.39 | 64 | 26.66 | 44 | 17.68 | 53 | 22.08 | 17 | 6.9 | 47 | 19.58 |
| አጠቃላይ ወንድና ሴት | | 91 | | 18.72% | | 114 | | 23.45% | | 124 | | 25.51% | | 97 | | 19.95% | | 64 | | 13.16% | |

ከላይ በሠንጠረዥ 3 እንደ ተመለከትነው ተጠኚዎች የፅሁፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ስድስት ዝርዝር ብልሃቶችን የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ምላሾች ተካፍሎ በመቶኛ ተተንትኗል።

ጥያቄ 13 በማነብበት ወቅት የፅሁፍ ይዘት መገመት፣የፅሁፉን አወቃቀር መመልከት ነባር አጠቃላይ እውቀትን መጠቀምና ግንኙነት መመስረት የመሳሰሉ ክንውኖችን አካሄዳለሁ  የሚለውን ወንድ 10(24.39%)ና ሴት 4(10%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 11(26.82%) ሴት8(20%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 8(19.51%) ሴት 12(30%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 9(21.95%) ሴት 10(25%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31%) ሴት 6(15%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት  ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል።

ጥያቄ 14 በማነበው ፅሁፍ ውስጥ ያለውን የሀሳብ ትስስር እለያለው የሚለውን ወንድ 8(19.51%)ና ሴት 9(22.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 15(36.58%) ሴት9(22.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት 7(17.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 6(14.63%) ሴት 12(30%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 2(4.87) ሴት6(15%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በተወሰኑት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል።

ጥያቄ 15 በማንበው ፅሁፍ ውስጥ የማገኛቸው ፍንጭ ሰጪ ቃላትና ሀራጋት የምንባቡን መልዕክት ለመረዳት ያግዙኛል የሚለውን ወንድ 15(23.58%)ና ሴት 12(30)% የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 12(29.26%)ና ሴት 8(20)% አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 6(14.68%) ሴት10(25%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 6(14.63%) ሴት 4(10%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 2(4.87) ሴት 6(15%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 16 በማነብበት ወቅት በፅሁፍ ውስጥ በቀረበው መረጃ ላይ ብቻ ከማተኮር ይልቅ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር በተያያዘ ያለኝን ዳራዊ ዕውቀትና የግል ልምድ ለማዛመድ እሞክራለሁ የሚለውን ወንድ 11(26.82%)ና ሴት 2(5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 12(29.26%) ሴት 5(12.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 5(12.19%) ሴት 10(25%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 9(21.95%) ሴት 8(20%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 4(9.75) ሴት 15(37.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 17 በማነብበት ወቅት በተለያዩ የፅሁፉ አንጓዎች መካከል በቀረቡ ሀሳቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ለመለየት ጥረት አደርጋለሁ  የሚለውን ወንድ 3(7.31%)ና ሴት 4(10%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት 8(20%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 18(43.9%) ሴት 5(12.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 7(17.07%) ሴት 13(32.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 10(25%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 18 በማንበብ ሂደት ከመረጃዎች በመነሳት የመወሰን ብልሃትን በመተግበር በመስመሮች መካከል ለማንበብ ጥረት አደርጋለሁ የሚለውን ወንድ 8(19.51%)ና ሴት 5(12.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት6(15%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 13(31.7%) ሴት 16(40%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 7(17.07%) ሴት 6(15%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 4(10%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት  ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በአካካሽ ብልሃት በፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ንዑስ የአንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ ለ(6) ጥያቄዎች ብዛት ናሙና ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 55(22.35%) አብዛኛውን ጊዜ 70(28.45%) አንዳንድ ጊዜ 60(24.39%) አልፎ አልፎ 44(17.88%) በፍፁም አልጠቀምም 17(6.9%) ሲሆን የሴቶች ናሙና 40(49.4%) ሁልጊዜ 36(15%) አብዛኛውን ጊዜ 44(18.33%) አንዳንድ ጊዜ 64(26.66%) አልፎ አልፎ 53(22.08%) በፍፁም አልጠቀምም 47(19.58%) የሁለቱ ፆታ ድምር ናሙና 81(46%) ሁልጊዜ 91(18.72%) አብዛኛውን ጊዜ 1148(23.45%)አንዳንድ ጊዜ 124(25.51%) አልፎ አልፎ 97(19.95%) በፍፁም አልጠቀምም 64(13.16%) ውጤት የተገኘ ሲሆን በወንዶችና ሴቶች መካከል በተሰጡት አማራጮች የብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት መታየቱን እና ልይነቱም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ብልሃቱን መጠቀማቸውን ይገልፃል።

## 4.2. የኢ ቀጥተኛ ብልሃቶች ትንተና

አንብቦ የመረዳት ብልሃት ለመማር ተገቢ የሆኑ ኢ ቀጥተኛ ብልሃቶችም የስሜት ነኪ፣ልዕለ አእምሯዊና ማህበራዊ ብልሃቶች በሚባሉ በሶስት ንዑሳን ምድቦች የሚከፋፈሉ ናቸው። በልዕለ አእምሯዊና ማህበራዊ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ተሰብስቧል። መረጃው እንደሚያመለክተው የተምሪዎች ኢ ቀጥተኛ የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው በተመጣጣኝ ደረጃ መጠቀማቸው ተረጋግጧል። በሁለቱ ንዑሳን ምድቦች ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር ብልሃቶች መረጃ እንዲሰጡ 12 በፅሁፍ መጠይቅ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ቀርበላቸዋል። እያንዳንዳቸው የኢ ቀጥተኛ ንዑሳን የመማር ብልሃቶች ስድስት ስድስት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹም 19-24 ልዕለ አእምሯዊ 25-30 ማህበራዊ ቢሆኑም አጠቃላይ ለተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ የተሰጠው ጥያቄ ባዛት 30 ሲሆን 40% የኢ ቀጥተኛ የመማር ብልሃት ነው (የእያንዳንዱን ጥያቄዎች ዝርዝር ከአባሪ አንድ ይመልከቱ)። በእያንዳንዱ ጥያቄዎች ስር አምስት አማራጮች ቀርበዋል።በቀረቡት ጥያቄዎች 1.በፍፁም አልጠቀምም 2.አልፎ አልፎ 3.አንዳንድ ጊዜ 4.አብዛኛውን ጊዜና 5.ሁልጊዜ ሲሆኑ የመለሱትን የመረጃ ትንተናና ማብራሪያ እያንዳንዱ ንዑሳን ብልሃቶች በጥናቱ ዓላማ መሰረት ተተንትኗል።

### 4.2.1. የልዕለ አእማሯዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሃቶች የሚመለከቱ መልስ እንዲሰጡ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርበላቸው ነበር። ተማሪዎች የመለሱት ምላሾች በቁጥር (ዝርዝሩን ከአባሪ ሰባት ይመልከቱ) በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ስድስት የልዕለ አእምሯዊ ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር በመቶኛ ተተንትኗል።

## ሠንጠረዥ 4. ልዕለ አእምሯዊ ብልሃቶች መረጃ

| ተቁ | ብልሃቶች | አምራጮች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁሌጊዜ | | | | አብዛኛውን ጊዜ | | | | አንዳንድ ጊዜ | | | | አልፎ አልፎ | | | | በፍፁም አልጠቀምም | | | |
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. | በማነበው ሁሉ ለመረዳት አልቸገርም፡፡ | 9 | 21.95 | 8 | 20 | 10 | 24.39 | 8 | 20 | 10 | 24.39 | 11 | 27.5 | 6 | 14.63 | 9 | 22.5 | 6 | 14.63 | 6 | 15 |
| 2. | ያነበብኩትን ምንባብ የበለጥ ለመረዳት በራሴ አገላለፅ እፅፈዋለሁ ወይም እናገረዋለሁ፡፡ | 9 | 21.9 | 8 | 20 | 16 | 39.02 | 15 | 30 | 8 | 19.51 | 5 | 12.5 | 5 | 12.19 | 8 | 20 | 3 | 7.31 | 8 | 20 |
| 3. | ምንባቡን ከማንበቤ በፊት የማከናውናቸውን ተግባራት አስቀድሜ አቅዳለሁ፡፡ | 6 | 14.65 | 8 | 20 | 14 | 34.14 | 8 | 20 | 11 | 26.82 | 8 | 20 | 2 | 4.87 | 2 | 5 | 5 | 12.19 | 8 | 20 |
| 4. | ምንባቡን በማነብበት ጊዜ ትኩረት ሳጣ ወደ ኋላ ተመልሼ አነባለሁ፡፡ | 14 | 34.34 | 10 | 25 | 11 | 26.82 | 9 | 22.5 | 6 | 14.63 | 5 | 12.5 | 8 | 19.51 | 10 | 25 | 2 | 4.87 | 6 | 15 |
| 5. | ለማንበብ በቀረበ ፅሁፍ ውስጥ በጥልቀት የማነበውን እና ብዙ ትኩረት የማንሰጥበትን ሀሳብ በመለየት አነባለሁ፡፡ | 7 | 17.07 | 9 | 22.5 | 14 | 34.14 | 6 | 15 | 10 | 24.39 | 12 | 30 | 4 | 9.75 | 3 | 7.5 | 6 | 14.63 | 10 | 25 |
| 6. | ምንባቡን አንብቤ ምን ያህል እንደተረዳሁ እና መልመጃዎችን በመስራት ዙሪያ ያሳየሁትን ማሻሻል | 13 | 31.7 | 9 | 22.5 | 17 | 41.46 | 13 | 32.5 | 2 | 4.87 | 3 | 7.5 | 6 | 14.63 | 9 | 22.5 | 3 | 7.31 | 6 | 156 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በራሴ እገመግማለሁ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | 61 | 24.79 | 52 | 21.66 | 82 | 33.33 | 59 | 24.58 | 47 | | 44 | 18.33 | 31 | 12.6 | 41 | 17.08 | 25 | 10.16 | 44 | 18.33 |
| አጠቃላይ ወንድና ሴት | | 101 | | 20.78% | | 138 | | 28.39% | | 91 | | 18.72 % | | 72 | | 14.81 % | | 69 | | 14.19% | |

ከላይ በሠንጠረዥ 4 እንደ ተመለከትነው ተጠኚዎች የፅሁፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ስድስት ዝርዝር ብልሃቶችን የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ምላሾች ተካፍሎ በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

ጥያቄ 19 በማነበው ሁሉ ለመረዳት አልቸገርም የሚለውን ወንድ 9(26.95%)ና ሴት 8(20%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት8(20%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 10(24.38%) ሴት 11(27.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 6(14.63%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 6(14.63%) ሴት 6(15%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት  ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 20 ያነበብኩትን ምንባብ የበለጥ ለመረዳት በራሴ አገላለፅ እፅፈዋለሁ ወይም እናገረዋለሁ የሚለውን ወንድ 9(21.95%)ና ሴት 8(20%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 16(39.02%) ሴት15(30%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 8(19.51%) ሴት 5(12.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 5(12.19%) ሴት 8(20%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31 ሴት 8(20%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት  ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 21 ምንባቡን ከማንበቤ በፊት የማከናውናቸውን ተግባራት አስቀድሜ አቅዳለሁ የሚለውን ወንድ 9(21.95%)ና ሴት 8(20)% የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 14(34.14%) ሴት8(20%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 11(26.82%) ሴት 8(20%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 2(4.87%) ሴት 2(5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 5(12.19) ሴት 8(20%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት በተወሰነ መልኩ ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 22 ምንባቡን በማነብበት ጊዜ ትኩረት ሳጣ ወደ ኋላ ተመልሼ አነባለሁ የሚለውን ወንድ 14(34.34%)ና ሴት 10(25%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 11(26.82%) ሴት

9(22.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 6(14.63%) ሴት 5(12.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 8(19.51%) ሴት 10(25%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 2(4.87) ሴት 6(715%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 23 ለማንበብ በቀረበ ፅሁፍ ውስጥ በጥልቀት የማነበውን እና ብዙ ትኩረት የማንሰጥበትን ሀሳብ በመለየት አነባለሁ የሚለውን ወንድ 7(17.07%) ሴት 9(22.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ 14(34.14%)ና ሴት 6(15%) ወንድ አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት 12(30%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 4(9.75%) ሴት 3(7.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 6(14.63) ሴት 10(25%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 24 ምንባቡን አንብቤ ምን ያህል እንደተረዳሁ እና መልመጃዎችን በመስራት ዙሪያ ያሳየሁትን ማሻሻል በራሴ እገመግማለሁ የሚለውን ወንድ 13(31.7%)ና ሴት 9(22.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 17(41.46%) ሴት 13(32.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 2(4.87%) ሴት 3(7.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 6(14.63%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 3(7.31) ሴት 6(15%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱ ፆታዎች የየተናጠል ውጤት ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በልዕለ አእምሯዊ ብልሃት በፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ንዑስ የአንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ ለ(6) ጥያቄዎች ብዛት ናሙና ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 61(24.79%) አብዛኛውን ጊዜ 82(33.33%)አንዳንድ ጊዜ 47(19.1%) አልፎ አልፎ 31(12.60%) በፍፁም አልጠቀምም 25(10.18%) ሲሆን የሴቶች ናሙና 40(49.4%) ሁልጊዜ 52(21.66%) አብዛኛውን ጊዜ 59(24.58%) አንዳንድ ጊዜ 44(18.33%) አልፎ አልፎ 41(17.08%) በፍፁም አልጠቀምም 44(18.33%) የሁለቱ ፆታ ድምር ናሙና 81(46%) ሁልጊዜ 101(20.78%) አብዛኛውን ጊዜ 138(28.39%)አንዳንድ ጊዜ 91(18.72%) አልፎ አልፎ 72(14.81%) በፍፁም አልጠቀምም 69(14.19%) ውጤት የተገኘ ሲሆን በወንዶችና ሴቶች መካከል በተሰጡት አማራጮች የብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት መታየቱን እና ልይነቱም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ብልሃቱን መጠቀማቸውን ይገልፃል፡፡

### 4.2.2. ማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

ተማሪዎች የዚህን ዝርዝር ብልሃቶች የሚመለከቱ መልስ እንዲሰጡ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው ነበር፡፡ ተማሪዎች የመለሱት ምላሾች በቁጥር (ዝርዝሩን ከአባሪ ሰባት ይመልከቱ) በእያንዳንዱ አማራጭ ስር ስድስት የማህበራዊ ጥያቄ የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

## ሠንጠረዥ 5. ማህበራዊ ብልሃቶች መረጃ

| ተቁ | ብልሃቶች | አምራጮች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁልጊዜ | | | | አብዛኛውን ጊዜ | | | | አንዳንድ ጊዜ | | | | አልፎ አልፎ | | | | በፍፁም አልጠቀምም | | | |
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. | በማነብበት ወቅት ተማሪዎችን እንዲያስተካክሉኝ እጠይቃቸዋለሁ፡፡ | 10 | 24.39 | 4 | 10 | 14 | 34.14 | 9 | 22.5 | 5 | 12.19 | 8 | 20 | 5 | 12.19 | 8 | 20 | 7 | 17.07 | 11 | 27.5 |
| 2. | ማንበብ ከመጀመሬ በፊት በርዕሶቹ እና በንዑሳን ርዕሶች በቀረቡት ጉዳዮች ዙሪያ መወያየት ያስደስተኛል፡፡ | 6 | 14.63 | 7 | 17.5 | 16 | 39.02 | 10 | 25 | 7 | 17.07 | 11 | 27.5 | 10 | 24.39 | 6 | 15 | 2 | 4.87 | 6 | 15 |
| 3. | የአማርኛ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ፡፡ | 19 | 46.34 | 8 | 20 | 13 | 31.07 | 11 | 27.5 | 1 | 2.43 | 11 | 27.5 | 7 | 17.07 | 8 | 20 | 1 | 2.43 | 2 | 5 |
| 4. | ከአማርኛ ተናጋሪዎች ድጋፍ እጠይቃለሁ፡፡ | 6 | 14.63 | 5 | 12.5 | 7 | 17.07 | 10 | 25 | 10 | 24.39 | 4 | 10 | 11 | 26.82 | 7 | 17.5 | 7 | 17.07 | 14 | 35 |
| 5. | በማንበብ ሂደት የተወሰኑ አባላትን ባቀፉ ቡድኖች ውስጥ በመሆን በጋራ መስራት እና | 7 | 17.07 | 3 | 7.5 | 13 | 31.07 | 10 | 25 | 11 | 26.82 | 14 | 35 | 6 | 14.63 | 8 | 20 | 4 | 9.75 | 5 | 12.5 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መደጋገፍን በንቃት አካሂዳለሁ፡፡ | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| 6. | ከማንበብ ክዋኔ በፊት እኔ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በቅድመ ንባብ ተግባራት እንሳተፋለን፡፡ | 15 | 36.58 | 6 | 15 | 12 | 29.26 | 8 | 20 | 6 | 14.63 | 7 | 17.5 | 4 | 9.75 | 9 | 22.5 | 4 | 9.75 | 10 | 25 |
| | | 63 | 25.60 | 33 | 13.75 | 75 | 30.48 | 58 | 24.16 | 40 | 16.26 | 55 | 22.91 | 43 | 17.47 | 46 | 19.16 | 25 | 10.16 | 48 | 20 |
| አጠቃላይ ወንድና ሴት | | 96 | | 19.75% | | 133 | | 27.36% | | 95 | | 19.54 % | | 89 | | 18.31 % | | 73 | | 15% | |

ከላይ በሠንጠረዥ 5 እንደ ተመለከትነው ተጠኚዎች የፅሁፍ መጠይቁ ጥያቄዎች ስድስት ዝርዝር ብልሃቶችን የመለሱ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ድምር ለአጠቃላይ ምላሾች ተካፍሎ በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

ጥያቄ 25 በማነብበት ወቅት ተማሪዎችን እንዲያስተካክሉኝ እጠይቃቸዋለሁ የሚለውን ወንድ 10(24.39%)ና ሴት 4(10%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 14(34.14%) ሴት 9(22.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 5(12.19%) ሴት 8(20%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 15(12.19%) ሴት 8(20%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 7(17.07%) ሴት 11(27.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 26 ማንበብ ከመጀመሬ በፊት በርዕሶቹ እና በንዑሳን ርዕሶች በቀረቡት ጉዳዮች ዙሪያ መወያየት ያስደስተኛል የሚለውን ወንድ 6(14.63%)ና ሴት 7(17.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 16(39.02%) ሴት 10(25%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 7(17.07%) ሴት 11(27.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 10(24.39%) ሴት 6(15%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 2(4.87%) ሴት 6(15%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 27 የአማርኛ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ የሚለውን ወንድ 19(46.34%)ና ሴት 8(20%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 13(31.07%) ሴት 11(27.5%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 1(2.43%) ሴት 11(27.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 7(17.07%) ሴት 8(20%)

አልፎ አልፎ እና ወንድ 1(2.43%) ሴት 2(5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 28 ከአማርኛ ተናጋሪዎች ድጋፍ እጠይቃለሁ የሚለውን ወንድ 6(14.63%)ና ሴት 5(12.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 7(17.07%) ሴት 10(25%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 10(24.39%) ሴት 4(10%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 11(26.82%) ሴት 7(17.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 717.07(%) ሴት 14(35%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ልዩነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 29 በማንበብ ሂደት የተወሰኑ አባላትን ባቀፉ ቡድኖች ውስጥ በመሆን በጋራ መስራት እና መደጋገፍን በንቃት አካሂዳለሁ የሚለውን ወንድ 7(17.07%)ና ሴት 3(7.5%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 13(31.07%) ሴት 10(25%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 11(16.82%) ሴት 14(35%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 6(14.63%) ሴት 8(20%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 4(9.75%) ሴት 5(22.5%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ጥያቄ 30 ከማንበብ ክዋኔ በፊት እኔ ከክፍል ጓደኞቼ ጋር በመሆን በቅድመ ንባብ ተግባራት እንሳተፋለን የሚለውን ወንድ 15(36.58%)ና ሴት 6(15%) የሚያህሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ የሚጠቀሙ ወንድ 12(29.26%) ሴት 8(20%) አብዛኛውን ጊዜ ሲጠቀሙ ወንድ 6(14.63%) ሴት 7(17.5%) አንዳንድ ጊዜ፣ ወንድ 4(9.75%) ሴት 9(22.5%) አልፎ አልፎ እና ወንድ 4(9.75%) ሴት 10(25%) በፍፁም አልጠቀምም የሚል ሲሆን ከዚህ መረጃ እንደምንረዳ ወንድና ሴት በሁለቱም ፆታዎች መሀከል ስላላቸው የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በማህበራዊ ብልሃት በፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ንዑስ የአንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ ለ(6) ጥያቄዎች ብዛት ናሙና ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 63(25.60%) አብዛኛውን ጊዜ 75(30.48%)አንዳንድ ጊዜ 40(16.26%) አልፎ አልፎ 43(17.47%) በፍፁም አልጠቀምም 25(10.16%) ሲሆን የሴቶች ናሙና 40(49.4%) ሁልጊዜ 33(13.75%) አብዛኛውን ጊዜ 58(24.16%) አንዳንድ ጊዜ 55(22.91%) አልፎ አልፎ 46(19%) በፍፁም አልጠቀምም 48(20%) የሁለቱ ፆታ ድምር ናሙና 81(46%) ሁልጊዜ 96(19.75) አብዛኛውን 133(27.36) አንዳ አንድ ጊዜ

95(19.54) አልፎ አልፎ 89(18.31) በፍፁም አልጠቀምም 73(15) ውጤት የተገኘ ሲሆን በወንዶችና ሴቶች መካከል በተሰጡት አማራጮች የብልሃት አጠቃቀማቸው ላይ ልዩነት መታየቱን እና ልይነቱም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ብልሃቱን መጠቀሙን ይገልፃል፡፡

## 4.3 ለአማርኛ መምህራን አንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም የመረጃ ትንተና

ቀደም ሲል እንደ ተገለፀው የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች በአጥኚው በዝርዝር ተብራርቷል፡፡ ከተብራራላቸው በኋላ ግልፅ ያልሆነላቸው ነገር ካለ ጥያቄ እንዲያነሱ በማድረግ የተለያዩ ክፍት የፅሁፍ ጥያቄዎችን እና የተገኙ መልሶችን መሠረት በማድረግ በሚከተለው መልኩ ለሰባተኛ ክፍል መምህራን በቃለ መጠይቅ አማካይነት የቀረበውን በዝርዝር ለማብራራት ተሞክሯል፡፡ የሰባተኛ ክፍል መምህራን የተጠቀሱትን የጥያቄ አይነቶች በሙሉ የሰጡት ምላሾችም፦

ጥያቄ 1፦ በምንባብ ጊዜ ርዕሱን በማስነበብ ፅሁፉ ስለ ምን እንደሆነ እንዲገምቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?

ይህንን ጥያቄ ርዕሱን በማስነበብ ፅሁፉ ስለምን እንደሆነ እና የራሳቸውን ግምት ርዕሱን በማየት እንዲሰጡ ተማሪዎችን መጠየቃቸውን እና አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተጠየቁት ጥያቄ መሠረት ርዕሱን በመመልከት ምን ሊመጣ እንደሚችል የራሳቸውን ግምት ያስቀምጣሉ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 2፦ የቀረበን ምንባብ አንብበው የመረዳት ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?

አንድ ፀሀፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት በሚገባ መረዳታቸውን እንደ ሚጠይቁና ከግማሽ በታች የሚሆኑ ተማሪዎች አንድ ፀሀፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ለመረዳት እንደሚቸገሩ እና ደጋግመው እንደሚያነቡት የተወሰኑት ደግሞ ካልገባቸው ማንበቡን እንደሚተዉት ገልፀዋል፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ በጥያቄ ቁጥር አስራ ዘጠኝ የቀረበውን አካካሽ ብልሃት በአብዛኛው እንደማይጠቀሙበት ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

ጥያቄ 3. በፅሁፍ ውስጥ ፀሀፊው ማስተላለፍ የፈለገው ሀሳብ በራሳቸው መንገድ አሳጥረው እንዲፅፉ ያደርጋሉ?

የፅሁፍን ሀሳብ ከተረዱ በኋላ በራሳቸው የበለጠ ግልፅ እንዲሆንላቸው ፅሁፍን አሳጥረው እንዲፅፉ እናደርጋለን ነገር ግን ይህን ሲያደርጉ አብዛኞቹ አንብበው ከገባቸው በራሳቸው አገላለፅ እንዲፅፉ አንዳንዶች ደግሞ መፃፍ እንደ ማይፈልጉ ለማብራራት ችለዋል፡፡

ጥያቄ 4. ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው አንቀፆችን ሲያነቡ በአንቀፅ መካከል ወይም አንቀፁን እንደጨረሱ ማንበባቸውን ያቋርጣሉ?

ለዚህ ጥያቄ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ካልገባቸው ያቋርጣሉ ይሁን እንጂ የተወሰኑት ሀሳቡን ለመረዳት ወደኋላ ተመልሰው እንደሚያነቡ የተወሰኑት ደግሞ ይከብዳል በማለት እስከመጨረሻው ድረስ እንደሚያነቡ እና አቋርጠው እንደሚተውት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጥያቄ 5. በምንባብ ጊዜ ያነበቡትን ፅሁፍ አስቀድመው ከሚያውቁት(ከቀድመ ልምድ እና እውቀት ጋር) የመገንዘብ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?

ከምላሹ ለመረዳት እንደተቻለው በምንባብ ጊዜ ያነበቡትን ፅሁፍ አስቀድመው ከሚያውቁት የቀደሞ እውቀትን የመቀስቀስ ጥያቄዎችን እና ካነበቡት ጋር መገንዘባቸውን መጠየቃቸውን ገልፀዋል፡፡

ጥያቄ 6. ያነበቡትን ምንባብ የበለጠ እንዲረዱት በራሳቸው አገላለፅ እንዲገልፁት ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?

በዚህ ጥያቄ ዙሪያ መምህራን የሰጡት ምላሽ ያነበቡትን ምንባብ የበለጠ እንዲረዱት በራሳቸው አገላለፅ አንዳንዴ እንደሚጠይቁና አብዛኛው ተማሪዎች እንደሚፅፉት እና ውስኖቹ ደግሞ እንደማይረዱት ገልፀዋል፡፡

ጥያቄ 7. ከምንባብ ውስጥ ያለውን ዝርዝር እና ጠቃሚ መረጃ ፈልገው የማግኘት ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?

ከምላሹ ለመረዳት እንደተቻለው ከምንባቡ ውስጥ ያለውን ዝርዝር እና ጠቃሚ መረጃ ፈልገው የማግኘት ጥያቄዎችን መጠየቃቸውን ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ መምህሮቹም የንባብ ትምህርት ባለበት ሁሉ ቅድመ ጥያቄዎች ይኖራሉ ቅድመ ጥያቄዎቹንም በማንበብ የቀጣዩን ምንባብ ስለምን እንደሚያትት ለመረዳት እንዳይቸገሩ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል በምዕራፍ ሁለት እንደ ተጠቀሰው ትንበያ ማለት ለማንበብ የተመረጠውን ፅሁፍ ርዕስ በማየት ፅሁፉ ስለምን ሊገልፅ አንደሚችል እንዲሁም የፅሁፉን የተወሰነ ክፍል በማንበብ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን እየገመቱ የማንበብ ሂደት ነው (Grellet& Nuttall,1996)፡፡እንደ ምሁሮቹ አባባል በንባብ ትምህርት የተማሪዎችን የመተንበይ ክሂል ለማዳበር የሚያሥችሉ ጥያቄዎችን በአግባቡ ሊያካትቱ እንደ ሚገባቸው ይገልፃሉ፡፡ መምህሮቹ የሰጡት ምላሽ ከምሁሮቹ ሀሳብ ጋር የተጣጣመ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡

ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው አንቀፆችን ሲያነቡ በአንቀፁ መካከል ወይም አንቀፁን እንደጨረሱ ማንበባቸውን ያቋርጣሉ የተወሰኑት ተማሪዎች ሀሳቡን ለመረዳት ወደኋላ ተመልሰው ያነቡታል፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ሲከብዳቸው እስከ መጨረሻው ሳያነቡ ማቋረጣቸው፡፡

ምንባቡን አንብበው የመረዳት ጥያቄዎችን ተማሪዎች ምንባቡን ካነበቡ በኋላ ምን ያህል እንደተረዱ ጥያቄዎችን መጠየቃቸው ገልፀዋል። Smith (1985) አንድን ንባብ አንብቦ መረዳት የሚያስፈልገው ከምንባቡ የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስ በማሰብ እንደሆነ ያስረዳሉ። ምክንያታቸውም ከምሁሩ ሀሳብ ጋር የተጣጣመ ነው።

## 4.4 ቀጥተኛና ኢ ቀጥተኛ መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

### ሠንጠረዥ 6 የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች አጠቃቀም መረጃ

| ተ.ቁ | ብልሃቶች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሁል ጊዜ | | አብዛኛውን ጊዜ | | አንዳንድ ጊዜ | | አልፎ አልፎ | | በፍፁም አልጠቀምም | |
| | | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1. | አእምሯዊ | 98 | 20.16 | 147 | 30.24 | 96 | 19.75 | 94 | 19.34 | 51 | 10.49 |
| 2. | ትውስታ | 103 | 21.1 | 148 | 30.45 | 87 | 17.9 | 88 | 10.4 | 60 | 12.34 |
| 3. | አካካሽ | 91 | 18.72 | 114 | 23.45 | 124 | 25.51 | 97 | 19.95 | 64 | 13.16 |
| 4. | ልዕለ አእምሯዊ | 113 | 23.25 | 141 | 29.01 | 91 | 18.72 | 72 | 14.81 | 69 | 14.19 |
| 5. | ማህበራዊ | 96 | 19.75 | 133 | 27.36 | 95 | 19.54 | 89 | 18.31 | 73 | 15 |

ከላይ በሠንጠረዥ 6 እንደ ተመለከትነው ተጠኚዎች በሰጡት መረጃ የጥናቱ አንደኛው ዓላማ "ተማሪዎች የበለጠ የሚጠቀሙት የትኛውን ብልሃት ነው?" ለሚለው አእምሯዊ ሁልጊዜ 98(20.16) አብዛኛውን 147(30.24) አንዳ አንድ ጊዜ 96(19.75) አልፎ አልፎ 94(19.34) በፍፁም አልጠቀምም 51(10.49) ትውስታ ሁልጊዜ 103(21.1) አብዛኛውን 148(30.45) አንዳ አንድ ጊዜ 87(17.9) አልፎ አልፎ 88(10.4) በፍፁም አልጠቀምም 60(12.34) አካካሽ ሁልጊዜ 91(18.72) አብዛኛውን 114(23.45) አንዳ አንድ ጊዜ 124(25.51) አልፎ አልፎ 97(19.95) በፍፁም አልጠቀምም 64(13.16) ልዕለ አእምሯዊ ሁልጊዜ 113(23.25) አብዛኛውን 141(29.01) አንዳንድ ጊዜ 91(18.72) አልፎ አልፎ 72(14.81) በፍፁም አልጠቀምም 69(14.19) ና ማህበራዊ ሁልጊዜ 96(19.75) አብዛኛውን 133(27.36) አንዳ አንድ ጊዜ 95(19.54) አልፎ አልፎ 89(18.31) በፍፁም አልጠቀምም 73(15) የሚሉ ናቸው። በቀጥተኛ የቋንቋ የመማር ብልሃቶች ቋንቋን የሚማሩ ተማሪዎች ቀጥተኛ በሆኑ ጉዳዮች በተተኳሪው ቋንቋ መጠቀማቸውን የሚያመለክት በመሆኑ፣ በአንብቦ መረዳት ብልሃት

በትምህርቱ ሂደት በንቃት በመሳተፍ፣ እንዲሁም በአንብቦ መረዳት እና ኢ ቀጥተኛ በአንብቦ መረዳት ብልሃት ተማሪዎች የትምህርቱን ሂደት እንዴት ማስኬድ እንዳለባቸው የሚጠቁም ሂደት ከመሆኑ በተጨማሪ የመማር ማስተማሩ ሂደት አላማ እና እቅድ የሚነደፍበት፣ ሁኔታዎች የሚመቻቹበት ሂደት መሆናቸውን ከተማሪዎች በተሰበሰበው መረጃ ታይቷል፡፡ ተማሪዎቹ በአምስቱ የማንበብ ንዑሳን ክሂሎች ባላቸው ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ከአምስቱ አማራጮች ሁልጊዜና አባዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ሲደለደሉ ይህ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተጠኚዎች አብላጫ /ከፍተኛ/ ቁጥር ያላቸው ተጠኚዎች ብልሃቱን ሁልጊዜ መጠቀማቸውን ልዕለ አእምሯዊ 113(23.8)፣ ትውስታ 103(21.1)፣ አእምሯዊ 98(20.1)፣ ማህበራዊ 96(19.75)ና አካካሽ 91(18.72) ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ተጠኚዎች በአምስቱም ብልሃት አጠቃቀማቸው ከተሰጡት ብልሃት አማራጮች አብላጫ(ከፍተኛ) ቁጥር ያላቸው ተጠኚዎች ብልሃቱን ሁልጊዜና አብዛኛውን ጊዜ መጠቀማቸው ከፍተኛ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ እንዲሁም አምስቱንም የአንብቦ መረዳት ብልሃቶች በተመጣጣኝ ደረጃ ይጠቀማሉ ማለት ነው፡፡

በመሆኑም Oxford (2003) ማንበብን የመማር ብልሃቶች የቋንቋ ተማሪዎች በማንበብ ትምህርት ሂደት የንባብ ተግባራትን በማካሄድ የሚገለገሉባቸው ክንዋኔዎች፣ ልምዶች ወይም ስልቶች ሲሆን፣ እነዚህም ማንበብን የመማር ብልሃቶች በእያንዳንዱ ግለሰብ አእምሮ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የአሰራር ፀባዮች እንደሆኑ ያሥረዳሉ፡፡ ተማሪዎች ብልሃቶችን በመጠቀም በአማርኛ የንባብ ብልሃት አጠቃቀም ተግባራት ልምዶች ክንዋኔዎች በተመጣጣኝ ሁኔታ መጠቀማቸው ታይቷል፡፡ ልዕለ-አእምሯዊ ብልሃት ተማሪዎች በራሳቸው የሚማሩበትን መንገድ የሚያስተካክል ሲሆን እውቀትን እና የግንዛቤያችንን ሂደት የሚቆጣጠር ነው (Oxford 1990):: Papaleontious-Louca (2003) ልዕለ-አእምሯዊ ብልሃት ሁሉንም የግንዛቤ ደረጃ እነዚህም በራስ አስተሳሰብ ስለ አንድ ነገር የሚሰማን፣ ስለ አንድ ነገር ማሰብ በመከታተል እና በመቆጣጠር ምላሽ መስጠትን እንደሚያካትት ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ጥናትም በአውንታዊ ጎናቸው ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ሲደለደል የተማሪዎች አጠቃቀም መጀመሪያ ላይ ልዕለ አእምሯዊ እንደመሆኑ ተማሪዎች የሚማሩበትን ስለ አንድ ነገር ምላሽ መስጠቱን የሚያሳይ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በብልሃቱ ምንም አይነት ልዩነት ያለማስከተሉ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡

## 4.5 ፆታና አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች መረጃ ትንተናና ማብራሪያ

በሴትና በወንድ ተማሪዎች መካከል ጉልህ የሆነ የአንብቦ መረዳት ብልሃት አጠቃቀም መኖር አለመኖር ለሚለው ሁለተኛ ዓላማው ለእነዚህ መልስ ለማግኘትም በፅሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ በአእምሯዊ ብልሃት በፅሁፍ መጠይቅ የተማሪዎች ንዑስ የአንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀም በመቶኛ ተሰልቶ ለ(6) ጥያቄዎች ብዛት ናሙና ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 49(19.91%) አብዛኛውን

ጊዜ 86(35.8%) አንዳንድ ጊዜ 45(18.29%) አልፎ አልፎ 46(18.69%) በፍፁም አልጠቀምም 20(8.13%) ሲሆን የሴቶች ናሙና 40(49.3%) ሁልጊዜ 49(20.4%) አብዛኛውን ጊዜ 61(25.45%) አንዳንድ ጊዜ 51(21.25%) አልፎ አልፎ 48(20%) በፍፁም አልጠቀምም 31(12.91%)፣ በትውስታ ወንድ ሁልጊዜ 46(18.69%) አብዛኛውን ጊዜ 86(34.95%)አንዳንድ ጊዜ 45(18.29%) አልፎ አልፎ 42(17.07%) በፍፁም አልጠቀምም 27(10.97%) ሴት ሁልጊዜ 57(23.75%) አብዛኛውን ጊዜ 62(25.83%) አንዳንድ ጊዜ 42(10.5%) አልፎ አልፎ 46(19.16%) በፍፁም አልጠቀምም 33(13.75%)፣አካካሽ ወንድ 41(50.6%) ሁልጊዜ 55(22.35%) አብዛኛውን ጊዜ 70(28.45%) አንዳንድ ጊዜ 60(24.39%) አልፎ አልፎ 44(17.88%) በፍፁም አልጠቀምም 17(6.9%) ሲሆን ሁልጊዜ 36(15%) አብዛኛውን ጊዜ 44(18.33%) አንዳንድ ጊዜ 64(26.66%) አልፎ አልፎ 53(22.08%) በፍፁም አልጠቀምም 47(19.58%)፣ ልዕለ አእምሯዊ ወንድ ሁልጊዜ 58(23.57%) አብዛኛውን ጊዜ 79(32.11%) አንዳንድ ጊዜ 47(19.1%) አልፎ አልፎ 31(12.60%) በፍፁም አልጠቀምም 25(10.18%) ሲሆን የሴቶች ሁልጊዜ 43(17.91%) አብዛኛውን ጊዜ 59(24.58%) አንዳንድ ጊዜ 44(18.33%) አልፎ አልፎ 41(17.08%) በፍፁም አልጠቀምም 44(18.33%)ና ማህበራዊ ወንድ ሁልጊዜ 63(25.60%) አብዛኛውን ጊዜ 75(30.48%)አንዳንድ ጊዜ 40(16.26%) አልፎ አልፎ 43(17.47%) በፍፁም አልጠቀምም 25(10.16%) ሲሆን ሴት ሁልጊዜ 33(13.75%) አብዛኛውን ጊዜ 58(24.16%) አንዳንድ ጊዜ 55(22.91%) አልፎ አልፎ 46(19%) በፍፁም አልጠቀምም 48(20%) ሲሆን አጠቃላይ የሁለቱ ፆታዎች ልዩነት በሠንጠረዥ 7 ቀርቧል፡፡

## ሠንጠረዥ 7 የሁለቱ ፆታዎች ልዩነት

| ተ.ቁ | አማራጮች | ወንድ | መቶኛ | ሴት | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሁልጊዜ | 274 | 22.27 | 225 | 18.75 |
| 2. | አብዛኛውን ጊዜ | 399 | 32.43 | 285 | 23.75 |
| 3. | አንዳንድ ጊዜ | 237 | 19.3 | 253 | 21.08 |
| 4. | አልፎ አልፎ | 206 | 16.74 | 234 | 19.5 |
| 5. | በፍፁም አልጠቀምም | 114 | 9.26 | 203 | 16.92 |
| ጠቅላላ | | 1230 | 100 | 1200 | 100 |

ከላይ በሠንጠረዥ 7 የቀረበው በሁለቱ ፆታዎች መሀከል ያለው ልዩነት መጠን እኩል መሆን አለመሆን አምስቱንም ንዑስ የብልሃት አጠቃቀማቸውን ሲሆን ተማሪዎች አምስቱንም ብልሃቶች

ሴትና ወንድ ተማሪዎች ድምር በቁጥርና ምላሽ ተማሪዎች ለአጠቃላይ ምላሽ ተካፍሎ በመቶኛ ተተንትኗል፡፡ በትንተናው መሰረትም ጠቅላላ አምስቱንም ብልሃት ሁልጊዜ ወንድ 274(22.27) ሴት 225(18.75) በመሆኑ ልዩነታቸው ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ወንድ 399(32.43) ሴት 285(23.75) በመሆኑ ልዩነታቸው መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወንድ 237(19.3) ሴት 253(21.08) ልዩነታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ብልሃቱን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ ወንድ 206(16.74) ሴት 234(19.5) ልዩነታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ብልሃቱን በፍፁም የማይጠቀሙ ተማሪዎች ደግሞ ወንድ 114(9.26) ሴት 203(16.92) በመሆኑ መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

